# በሊባኖስ ለሚገኙ የውጭ ዜጋ የቤት ውስጥ ሰራተኞች የተቀናበረ የመረጃ ምንጭና መምሪያ

የሊባኖስ ሪፐብሊክ

የሠራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር

በዓለም የሥራ ድርጅት የአረብ አገራት

ክፍለ አህጉራዊ ጽ/ቤት

## በሊባኖስ ለሚገኙ የውጭ ዜጋ የቤት ውስጥ ሠራተኞች

## የተቀናበረ የመረጃ ምንጭና መምሪያ

በዓለም የስራ ደርጅት ታትመው በሚወጡ ጽሁፎች ውስጥ የሚገኙት ምልክቶች ከተባበሩት መንግስታት አሠራር ጋር የሚጣጣሙ ሲሆን እነዚሁ ምልክቶች እንዲሁም በተጠቀሱት ጽሁፎች ዉስጥ የሚገኙት የጽሁፍ አቀራረብ ዘዴዎች (መንገዶች) የማንኛውንም ሀገር ሕጋዊ አቋም፤ ስፋት ወይም ግዛት ወይም የአገሪቱን ባለስልጣናት ወይም የድንበር ይዞታን መከለል በተመለከተ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በዓለም የስራ ድርጅት አስተያየት የተሰጠ መሆኑን አያመለክትም::

ግለሰቦች በሚያዘጋጇቸው ጽሁፎች ጥናቶችና ሌሎች መሰል አስተዋጽኦዎች ውስጥ ለሚሰጡ አስተያየቶች ደራሲዎቻቸው ኃላፊዎች ናቸው:: እንደዚሁም የእነዚህ አስተዋጽኦዎች መታተም በውስጣቸው የያዟቸው አስተያየቶች የዓለም የስራ ድርጅት መቀበሉን አያረጋግጥም::

የንግድ ድርጅት ስሞች እንዲሁም ለሽያጭ የሚቀርቡ ምርቶችና የምርት ሂደቶች መጠቀስ በዓለም የስራ ድርጅት ተቀባይነት ማግኘትን የማያረጋግጥ ሲሆን በአንጻሩም የአንድ ንግድ ድርጅት ለንግድ የሚቀርብ ምርት ወይም የምርት ሂደት አለመጠቀስ ተቀባይነት አለማግኘትን አያሳይም::

ይህን የመረጃ ምንጭ እና መምሪያ በአብዛኛው ላኪ በሆኑ አገሮች (አዲስ አበባ፤ ኮሎምቦ፤ ሃኖይ፤ ካትማንዱ እና ማኒላ) ከሚገኙ የዓለም የስራ ደርጅት (አይ. ኤል. ኦ.) ጽ/ቤቶች እንዲሁም ቤይሩት ከሚገኘው የዓለም የስራ ድርጅት የአረብ አገራት ክፍለ አህጉራዊ ጽ/ቤት ማግኘት ይቻላል::

ይህ የተደራጀ የመረጃ ምንጭና መምሪያ በአስራ ሁለት ቋንቋዎች (በአማርኛ፤ በአረብኛ፤ በቤንጋሊ፤ በባሃሳ፤ በኢንዶኔዥያ፣ በእንግሊዝኛ፤ በፈረንሳይኛ፡ በማላጋሲ፤ በኔፓሊ፤በሲንሃሌሴ፤ በታጋሎግ፤ በታሚል እንዲሁም በቬትናምኛ) የተዘጋጀ ከመሆኑም በላይ ከዋና ዋና ላኪ አገሮች ወደ ሊባኖስ በመጡ ሴት ስደተኛ የቤት ውስጥ ሰራተኞች ላይ ሙከራ ተደርጎበታል::

ለዚህ ህትመት የዋለው ገንዘብ የተገኘው በዓለም የሥራ ድርጅት የአረብ አገራት ክፍለ አህጉራዊ ጽ/ቤት፤ እንዲሁም የዓለም የስራ ድርጅት የስርዐተ ጾታ እኩልነት ቢሮ፤የአውሮፓ ህብረት እና የተባበሩት መንግስታት የሴቶች ልማት ፈንድና የአረብ አገራት ክፍለ አህጉራዊ ጽ/ቤት ነው::

ይህ የመረጃ መምሪያ ያለ ክፍያ በነጻ የሚታደል ነው::

## ለበለጠ መረጃ በዚህ አድራሻ ያግኙን፡፡


**በዓለም የሥራ ድርጅት የአረብ አገራት**

**ክፍለ አህጉራዊ ጽ/ቤት**

**አሬስኮ ማእከል፤ ጀስቲንየን ጎዳና ፡ ካንታሪ**

ስልክ፡- +961 (0)1 752400

ፋክስ፡- +961 (0)1 752405

ኢ. ሜይል: beirut@ilo.org.lb

**አይ ኤል ኦ - ሀኖይ**

ስልክ፡- +84 4 734 0900

ፋክስ፡- +84 4 734 0904

ኢ. ሜይል: hanoi@ilohn.org.vn

**አይ ኤል ኦ - አዲስ አበባ**

ስልክ፡- +251-11-544-4480, +251-11-544-4481

ፋክስ፡- +251-11-544-5573, +251-11-551-3633

ኢ. ሜይል: addisababa@ilo.org

**አይ ኤል ኦ - ካትማንዱ**

ስልክ፡- +977 1 55 55 771

ፋክስ፡- +977 1 55 50 714

ኢ. ሜይል: kathmandu@ilo.org

**አይ ኤል ኦ - ኮሎምቦ**

ስልክ፡- +94 11 259 2525

ፋክስ፡- +94 11 250 0865

ኢ. ሜይል: colombo@ilo.org

**አይ ኤል ኦ - ማኒላ**

ስልክ፡- + 632 580.9900

ፋክስ፡- + 632 580.9999

ኢ. ሜይል: manila@ilo.org

ማውጫ ገጽ

**መቅድም ....................................................................... 2**

**ውድ ሠራተኛ ሆይ ................................................................ 3**

**ይህን መመሪያ ለመረዳት፡- ................................................ 4**

**ምዕራፍ አንድ ................................................................... 6**

**የውጪ ዜጋ ሠራተኛ ወደ ሊባኖስ መጓዝ ................................ 6**

1. ወደ ሊባኖስ ከመጓዝህ(ሽ) በፊት ........................................ 7

ወደ ሊባኖስ ከመጓዝህ(ሽ) በፊት መታወቅ ያለባቸው ነጥቦች ................ 7

ሰንጠረዥ 1፡- የህክምና ምርመራ ሪፖርት ...................................... 9

ሰንጠረዥ 2፡- ምን መጠየቅ እንደሚገባሽ/ህ ለማሰብ የሚረዱ አንዳንድ ነጥቦች ........................................................ 11

2. ሊባኖስ ከደረስክ(ሽ) በኋላ .............................................. 12

ሊባኖስ ውስጥ ህጋዊ ለመሆን፡- ........................................ 12

3. ሊባኖስ ከደረስክ (ሽ) በኋላ የምታከናውኛ/ና/ቸው ዘጠኝ ነገሮች ........ 15

4. ከሊባኖስ መልቀቅ ስትፈልግ/ጊ ........................................... 16

**ምዕራፍ ሁለት ................................................................ 17**

**በሊባኖስ ዉስጥ እንደ ውጭ ዜጋ ......................................... 17**

1. የስራ ቅጥር ውልህ (ሽ) ምን ይላል ? .................................. 18

- ወርሀዊ ደመወዝ ........................................................ 18
- የስራ አፈጻጸም ባህርይ ................................................ 19
- ጥቅማ ጥቅም .......................................................... 19
- ህክምና ................................................................. 19
- የስራና የመኖርያ ፈቃዶች ............................................. 20
- የስራ ሰዐት ............................................................. 20
- ሳምንታዊ እረፍት ....................................................... 20

➢ የአመት እረፍት ....20
➢ የመጓጓዣ ወጪዎች ....20
➢ ከቤተሰብ ጋር ስለመገናኘት ....21
➢ የህመም ፍቃድ ....21
➢ የስራ ውል መቋረጥ ....21
➢ አለመግባባቶች ....22
➢ ቅጂዎች ....22

**ምዕራፍ 3 ....23**

**ችግር በሚገጥምሽ(ህ) ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚገባሽ(ህ) ....23**

1. በሊባኖስ በሕጋዊ መንገድ ለመኖር የሚፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ካልተሟሉ ችግር ውስጥ ገብተሻል ማለት ነው። ....24
   ➢ በሕጋዊ መንገድ የመኖር መብትን ሊያሳጡ የሚያበቁ ሁኔታዎች ....24
   ➢ በሕጋዊ መንገድ ለመኖር የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ሲጓደሉ ምን ይፈጠራል? ....24
2. አለመግባባት ሲነሳ ምን ማድረግ እንደሚገባ ....28
3. በሥራ ላይ የሚደርስ ጥቃት ምድንነው? ....29
4. አሰሪን ስለመቀየር ....30
5. የሕግ አገልግሎት ድጋፍ ....31
6. ተጨማሪ መረጃዎች ....32
   ➢ በሥራ ቦታ ላይ ደህንነትን ስለመጠበቅ ....32
   ➢ ስለ ጋብቻ ....33
   ➢ ስለ እርግዝና ....33
   ➢ "በሰዎች መነገድ" ....34

**ምዕራፍ 4 ....36**

**የሊባኖስን ባህል መለማመድ ....36**

1. ስለሊባኖስ፡- ስለ አገሩ ሁኔታ መግለጫ ....37

2. ባህላዊ ክንውኖች ........ 39

3. ከቀጣሪሽ(ህ) ቤተሰብ ጋር መዋሃድ ........ 40

4. ሃይማኖት ........ 40

5. ማህበራዊ ግብረገብነትና ባህርይ ........ 41

6. ምግብ ........ 42

7. የዕዳት ሁኔታ ደረጃ ........ 43

8. አገር ቤት ካሉ ዘመዶችሽ(ህ) ጋር እንዴት መገናኘት እንደሚቻል ........ 43

9. ገንዘብ ወደ አገር ቤት እንዴት እንደሚላክ ........ 46

10. ትራንስፖርት ........ 46

11. ገበያዎች ........ 48

**ውድ ሠራተኛ ሆይ ........ 49**

**አባሪዎች ........ 50**

አባሪ 1:- የዐረብኛ ቋንቋ ........ 51

አባሪ 2:- እርዳታ ስለመጠየቅ ........ 62

አባሪ 3:- የግል የቀን ማስታወሻ ........ 69

አባሪ 4:- ስለማህበራት የቅድመ-ጉዞ ሥልጠና እና በአገርሽ(ህ) ስለሚገኙ የስደተኞች ማህበራት የሚገልፅ ጠቃሚ መረጃ ........ 71

አባሪ 5:- የቤት ውስጥ መገልገያ መሣሪያዎችን፣ ማሽኖችንና የዕዳት መሣሪያዎችን ያለ ስጋት መጠቀም ........ 78

አሰሪሽን (ህ)ን መጠየቅ ስለሚያስፈልግባቸው ሁኔታዎች ........ 79

አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮች እነሆ፡- ........ 79

አባሪ 6:- ለህይወት የሚያስፈልጉ ክህሎቶች ........ 81

አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ማሳለፍ ........ 81

በአደጋ ጊዜ እንዴት መሆን እንዳለብሽ/ህ ........ 82

አባሪ 7:- የውጭ ሀገር የቤት ሰራተኞች የስራ ቅጥር ውል ........ 83

የሊባኖስ ሪፐብሊክ መንግስት የሰራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር ........ 83

የውጭ ሀገር የቤት ሰራተኞች የስራ ቅጥር ውል ........ 83

# መቅድም

በአግባቡ የሚተዳደር የሠራተኛ ፍሰት በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ወንዶችና ሴቶች ሥራና የሥራ እድሎችን የሚፈጥር በመሆኑ እና ለተቀባይ ሀገሮች የኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦ የሚያደርግ በመሆኑ ለላኪም ሆነ ለተቀባይ ሀገሮች ጥቅም ሊያስገኝ ይችላል::

በአሁኑ ጊዜ በዓለም ደረጃ ካሉት 90 ሚሊዮን ስደተኛ ሠራተኞች ገሚሶቹ ሴቶች ናቸው:: በተቀባይ ሀገሮች ዉስጥ በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው የሥራ ሁኔታ ብዙ ልዩነቶች አሉት፡፡ ሴቶች የሚሰሯቸው ስራዎች በአብዛኛው እንደ ህጻናት ሞግዚትነት፤ በሽተኞችን ፤የአካል ጉዳተኞችንና አዛውንቶችን የመንከባከብ ሥራ ናቸው፡፡ ምንም እንኳ ወደ ውጭ ሀገር ለስራ የሚሄዱ ሴት ሰራተኞች ብዙ ፈተናዎች የሚገጥሟቸው ቢሆንም ለስራ ከቦታ ቦታ መዘዋወር ለራሳቸው የሚኖራቸውን ግምት የሚሳድግ እንደዚሁም በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲችሉ አቅም የሚፈጥርላቸው ነው፡፡

የዓለም የስራ ድርጅት ስደተኛ የቤት ሰራተኞች ተገቢ የስራ ቅጥር ውል እንዲኖራቸው እና መልካም የስራ ሁኔታ የተመቻቸላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ከሊባኖስ ባለስልጣናትና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በሊባኖስ ውስጥ በአሳታፊ የፖሊሲ ምክክር ሂደት ላይ ሲሳተፍ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም ይህ መመሪያ በሊባኖስ ሰራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር የበላይ ጠባቂነት እ.ኤ.አ. በአፕሪል 2007 በተቋቋመው በሊባኖስ የሚገኙ የስደተኛ ሴት የቤት ውስጥ ሰራተኞች ጉዳይ ጥምር ብሄራዊ ኮሚቴ አባላት በጋራ ባደረጉት ጥረት የተገኘ ውጤት ነው፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ ምቹ የስራ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችሉ የውሳኔ ሃሳቦችን የሚያግዙ ዓለምአቀፍ ስምምነት እ.ኤ.አ. በሰኔ 2011 በተካሄደው 100 ኛው ዓለምአቀፍ የስራ ጉባኤ ላይ ፀድቋል፡፡ እነዚህ አዳዲስ ዓለምአቀፍ የስራ ደረጃዎች የቤት ውስጥ ሰራተኞችና መብት ለማስከበር ወደ ፊት የሚያራምዱ ታሪካዊ እርምጃዎች ናቸው፡፡ ጥረታችን በሊባኖስ የሚኖሩና የሚሰሩ የውጭ ዜጋ የቤት ሰራተኞችን ደህንነት በማስጠበቅ ረገድ ብዙ አስተዋፅኦ ያደርጋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

**ሚስስ ናዳ አል-ናሽፍ**
**በዓለም የሥራ ድርጅት የአረብ አገራት**
**ክፍለ አህጉራዊ ጽ/ቤት ዳይሬክተር**

**ሚስተር ሻርብል ነሃስ**
**የሊባኖስ መንግስት የሠራተኛ ጉዳይ**
**ሚኒስትር**

## ውድ ሠራተኛ ሆይ

አዲስ የህይወት ልምድ በሚሰጥሽ(ህ) ሁኔታ በሊባኖስ ውስጥ በሚገኘው አዲሱ ቀጣሪሽ(ህ) ቤት ለመኖርና ለመስራት በዝግጅት ላይ ነሽ(ህ) እንበል። የቀጣሪሽ(ህ) ማህበራዊ ኑሮና ባህላዊ ልምዶች ከአንተ(ቺ) የተለዩ ናቸው። ቀጣሪሽ(ህ) ማንነትሽ(ህ)ን እንዲረዳና እንደግለሰብና እንደሠራተኛም መብቶችሽ(ህ)ን እንዲያከብር የቀጣሪሽ(ህ)ን መብቶች መረዳትና ማክበር እንደሚያስፈልግሽ(ህ) ምንግዜም መዘንጋት የለብሽ(ህ)ም።

ይህ መምሪያ የተመሰረተው በሊባኖስ በስራ ላይ ባሉ ህጎችና ፖሊሲዎች ላይ እና የሰራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር እ.ኤ.አ. ማርች 16 ቀን 2009 ባጸደቀው የውጭ ዜጋ የቤት ሰራተኞች የስራ ውል ላይ ነው።(በአባሪ 7 ላይ ተያይዟል)።

ይህ መምሪያ፡-

- በሊባኖስ ውስጥ በምትሰሪ(ራ)በት ጊዜ ስለሚኖርሽ(ህ)መብቶችና ግዴታዎች እንደዚሁም መብቶችን እንዴት ማስከበርና ግዴታዎችን እንዴት መወጣት እንደሚገባ ያስረዳሻል(ሃል)። እንዲሁም
- ከአገሩ፤ ከህዝቡ፤ ከባህላዊ ልምዶቹና የኑሮ ዘይቤዎቹ ጋር እንድትለማመጂ(ድ) ይረዳሻል(ሃል)።

የሊባኖስ ቆይታሽ(ህ) መልካም እንዲሆንልሽ(ህ) እንመኛለን።

ይህን መመሪያ ለመረዳት፡-

ቀጥሎ ያሉትን ምልክቶች ሲመለከቱ፡-



በምታደርጊው/ገው ነገር ወይም ባለሽ/ህ/በት ሁኔታ አደጋ ላይ ስለሆንክ መንቃት አለብሽ/ህ፡፡



የምትጓዥው/ዘው በአደጋ ውስጥ ነው፡፡



አስተማማኝ ስለሆነ መጓዝ ትችያለሽ/ላለህ፡፡



ጽሁፉን በጥንቃቄ አንብቢ/ብ/፡፡

ጥሩ መረጃዎች፤ገለፃዎችና ሃሳቦች አሉት፡፡

በዓለምአቀፍ ስምምነቶችና የስራ ደረጃዎች ስለ ሰብዓዊ መብት የተጠቀሱትን መረጃዎች ታገናለሽ/ህ፡፡



በጥንቃቄ አንብቢ/ብ/፡፡ ጽሁፉ ጠቃሚ መረጃዎችን ይሰጥሻ/ሃ/ል፡፡




የተለመዱ ጥያቄዎችና ተግባራዊ ምላሾችን በተመለከተ ምክር ይሰጣል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# የውጪ ዜጋ ሠራተኛ ወደ ሊባኖስ መጓዝ

# 1. ወደ ሊባኖስ ከመጓዝህ(ሽ) በፊት



## ወደ ሊባኖስ ከመጓዝህ(ሽ) በፊት መታወቅ ያለባቸው ነጥቦች

እንደ ህጋዊ የውጭ ዜጋ የቤት ሠራተኛ ወደ ሊባኖስ ለመሄድ ራስሽን(ህን) እያዘጋጀህ(ሽ) ነው እንበል፡፡ ስለሆነም ከአገርሽ(ህ) ከመውጣትሽ(ህ) በፊት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መፈጸምሽ(ህ)ን ማረጋገጥ ያስፈልግሻል(ሃል)፡፡

| መፈጸም የሚገባሽ(ህ) | ተፈጽሟል | አልተፈጸመም |
|---|---|---|
| ➢ አስፈላጊዎቹ ህጋዊ የጉዞ ሰነዶችን ማዘጋጀት<br>▪ ፓስፖርት<br>▪ ቪዛ<br>▪ የህክምና ምስክር ወረቀት( ሰንጠረዥ አንድን ይመልከቱ)<br>▪ የተሟላ የስራ ውል | X | |
| 2. አገርሽ(ህ) ሆነሽ(ህ በፈረምሽ(ከ)ው ውል ውስጥ የተጠቀሱትን ውል ግዴታዎችና የስራ ሁኔታዎችን ማንበብሽ(ህ)ን እና መረዳትሽን እንዲሁም በውሉ ይዘት መስማማትሽ(ህ)ን | X | |

| | | |
|---|---|---|
| 3. ያሉት ሰነዶች በሙሉ ፎቶ ኮፒ መነሳታቸውን እንዲሁም ከዋናው ፎቶግራፎችህ ጋር ቅጂዎቹን ለቤተሰቦችሽ(ህ) እና ለጓደኞችህ መስጠትሽ(ህ)ን | X | |
| 4. በአገርሽ(ህ) ውስጥ ያለውን ቀጣሪ ኤጀንሲና በሊባኖስ የሚገኘውን አስቀጣሪ ኤጀንሲ አድራሻ እንዲሁም በሊባኖስ ያለውን ቀጣሪ አድራሻ ለቤተሰቦችሽ(ህ) እና/ወይም ለጓደኞችሽ(ህ) መስጠትሽ(ህ)ን | X | |
| 5. በሊባኖስ የሚገኘውን የአገርሽ(ህ)ን ኤምባሲ የስልክ ቁጥር እንዲሁም በዚህ መመሪያ በስተመጨረሻ ላይ የሚገኘውን የአስቸኳይ ጥሪ የስልክ ቁጥሮችን በቃልሽ(ህ) መያዝሽ(ህ)ን | X | |
| 6. ይህንን መመሪያ ሙሉ በሙሉ በደንብ ማንበብሽ(ን) እንዲሁም በውስጡ ያሉትን ፍሬ ሐሳቦች በአግባቡ መረዳትሽ(ህ)ን | X | |

**ሰንጠረዥ 1፡- የህክምና ምርመራ ሪፖርት**

ወደሊባኖስ ከመጓዝሽ(ህ) በፊትና እዚያ ከደረስሽ(ህ) በኋላ እንድታደርጊ(ግ) የምትጠየቂያ(ቃ)ቸው የጤና ምርመራዎች ከተለመደው የእርግዝና ምርመራ ሌላ የወባ፤የሳንባ ነቀርሳ፤የጉበትና በወሲባዊ ግንኙነት የሚተላለፉትን በሽታዎች ያካትታል፡፡

**ለግንዛቤዎ፡-**

**ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፡-** በደምና በደም ውጤቶች አማካይነት ( በመርፌ፤በስለት ነገሮች እና በደም ንክኪ)፤ ቫይረሱ ካለበት ሰው ጋር ልቅ የግብረ ስጋ ግንኙነት በመፈጸም፤ ቫይረሱ ያለባት ሴት በምትወልድበት ጊዜ ሊተላለፍ ይችላል፡፡እንደ ቀዶ ህክምና፤ የጥርስ ሕክምናና የሰውነትን መበሳት ለሚጠይቁ ህክምናዎች ንጽህናቸው ያልተጠበቀ መሳሪያዎችን በመጠቀም እንዲሁም በደም ስር የሚሰጡ መርፌዎችን በጋራ በመጠቀም ሊተላለፍም ይችላል፡፡ የሊባኖስ መንግስት ቪዛ ከመስጠቱ በፊት ከቫይረሱ ነጻ መሆንዎን የሚያሳይ የጤና ምርመራ ውጤት እንዲቀርብለት ይጠይቃል፡፡

**የሳንባ ነቀርሳ(ቲ.ቢ)፡-** የሳንባ ነቀርሳ አብዛኛውን ጊዜ ሳንባን እንዲሁም አጥንቶችን፤ መገጣጠሚያዎችን አንዳንዴም ቆዳን ጭምር ሊያጠቃ የሚችል ገዳይ በሽታ ነው፡፡ በበሽታው የተያዘ ሰው ሁሉ ላይታመም ይችላል፡፡ ምልክት የማያሳይ የሳንባ ነቀርሳ የትም የሚገኝ ሲሆን ማንም ሰው የበሽታው ተሸካሚ ሊሆን ይችላል፡፡ምልክቶቹም ከሶስት ሳምንታት በላይ የቆየ አክታ ያለው ሳል፤የደረት ላይ ህመምና በአክታ ላይ ደም መታየት ናቸው፡፡ በተጨማሪም ትኩሳት፤ የቅዝቃዜ ስሜት፤ለሊት ላይ ማላብ፤ የምግብ ፍላጎት መቀነስ፤ ክብደት መቀነስና መገርጣት ሲሆኑ በሽታው የያዛቸው ሰዎች በቀላሉ የድካም ስሜት ይሰማቸዋል፡፡

## ከጉዞ በፊት ማወቅ የሚያስፈልጉ ጠቃሚ መረጃዎች

- ከአንቺ(ተ) በፊት ወደ ሊባኖስ ወይም ወደ አረብ አገራት ለስራ ሄደው የነበሩ የምታውቂያቸው/ቃቸው ሰዎች ካሉ ከአገር ከመልቀቅሽ/ህ በፊትም ሆነ አዲሱ አገር ከገባሽ/ህ በኋላም ቢሆን አግኝተሽ/ህ ስለህይወት ተሞክሯቸው እንዲያወጉሽ/ህ ጠይቂያቸው/ጠይቃቸው፡፡ አስቀጣሪሽ/ህ ኤጀንሲ ስላለው ስም ደግሞ ከአገርሽ/ህ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር መረጃ እንዲሰጥሽ/ህ ጠይቂ/ቅ፡፡ በአገርሽ/ህ ውስጥ በመጥፎ የስራ አፈጻጸም ምክንያት ስማቸው በጥቁር መዝገብ የተያዘ ኤጀንሲዎች ይኖራሉ፡፡ ስለዚህ ሁኔታ መረጃ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ማግኘት ትችያለሽ/ህ፡፡ በተጨማሪም ሊባኖስ ዉስጥ ስለሚኖርሽ/ህ ስራ አስቀጣሪውን ኤጀንሲ መጠየቅ አትዘንጊ/ጋ፡፡
- ለቤት ሠራተኞች ስልጠና በአገርሽ/ህ ውስጥ የሚሰጥ ከሆነ ሥልጠናውን ውሰጂ/ድ፡፡(አባሪ 4ን ይመልከቱ)
- በአገር ቤት ካሉ ስደተኛ ሠራተኞችና ቤተሰቦቻቸውን ለመደገፍ ከሚሰሩ የስደተኛ ሠራተኞች ማህበራት፤ ከቤት ሠራተኞች ማህበራትና ከድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ፍጠሪ/ር፡፡ (አባሪ 4ን ይመልከቱ)




**ሰንጠረዥ 2፡- ምን መጠየቅ እንደሚገባሽ/ህ ለማሰብ የሚረዱ አንዳንድ ነጥቦች**

ከዚህ ቀደም በስደት ቆይተው ለሚያውቁ ሰዎች ወይም ጓደኞችሽ/ህ ልታቀርቢላቸው(ልታቀርብላቸው) የሚገቡ ጥያቄዎች፡-

- መጀመርያ ለስራ የመለመለሽ/ህ አስቀጣሪ ኤጀንሲ ስም ማን ይባላል; ኤጀንሲው ጥሩ ስም ያለው ይመስልሻል/ሃል;
- ስለምትሰሪበት/ስለምትሰራበት ቤትና ቤተሰብ ሁኔታ ግልጽ፤ ትክክለኛና እውነተኛ መረጃ ሰጥተውካል/ሻል;

ከአዲሱ ስራ ጋር ለመለማመድ እንዲረዳሽ/ህ በቀጥታ የአስቀጣሪውና ኤጀንሲ ተወካይ ጥያቄ ማቅረብም ትችያለሽ፡፡ ለምሳሌ፡-

- ቀጣሪዬ ባላትዳር ነው ;
- ልጆች አሉት/አሏት; ካሉት/ካሏት ስንት ናቸው; እድሜያቸውስ ;
- በቤተሰቡ ዉስጥ አካል ጉዳተኛ/ ተጧሪ/ ህመምተኛ/ ሰው አለ;
- ደመወዜ በየወሩ ነው የሚከፈለኝ; ከመጀመሪያው ወር ጀምሮስ ይከፈለኛል; ምን ያህል;
- በኮንትራት ውሉ ውስጥ የተጠቀሱት የቅጥር ሁኔታዎች ምንና ምን ናቸው;( መኝታዬ የት ነው; የእረፍት ቀን ይኖረኛል; ወዘተ) መፈጸም ያለብኝ ተግባራት ምንና ምን ናቸው;
- ችግር ቢገጥመኝ ለማን ነው የማሳውቀው;

## 2. ሊባኖስ ከደረስክ(ሽ) በኋላ



ሊባኖስ ለመግባት፤ ለመቆየትና ህጋዊ ሆኖ እንደውጪ ዜጋ ሠራተኛ ስራ ለመስራት እዚህ አገር በምትቆዩበት ጊዜ ሁሉ የሚያገለግል ሕጋዊ የሥራና የመኖርያ ፈቃድ ይዞ መመዘገብ ያስፈልግሻ(ሃ)ል፡፡ ይህን አለመፈጸም ሊያሳስርሽ(ህ) ወይም ከአገር መባረርን ሊያስከትልብሽ(ህ)ይችላል፡፡

### ሊባኖስ ውስጥ ህጋዊ ለመሆን፡-

### 1. ስፖንሰር ያስፈልግሻል(ሃል)፡፡

ወደ ሊባኖስ መግባት የሚቻለው በስፖንሰር አማካይነት( በካፋላ ) ነው፡፡ ስፖንሰርሽ (ካፊል) ቀጣሪሽ ሲሆን አሁን ሊባኖስ ውስጥ ባለው ህግ መሰረት እንደውጪ ዜጋ የቤት ውስጥ ሠራተኛ ለመስራት እና ሕጋዊ ሆኖ ለመኖር የምትችይው(ለው) በዚህ መንገድ ብቻ ነው፡፡

### 2. ሕጋዊ የመግቢያ ቪዛና ፓስፖርት ያስፈልግሻ/ሃ/ል፡፡

የግል ሰነዶችሽ/ህ ( ቪዛ፤ ፓስፖርት፤ የመኖርያና የስራ ፈቃድ) በየወቅቱ መታደሳቸውና ጊዜ እንዳላለፈባቸው አረጋግጪ/ጥ፡፡ ይህ የቀጣሪሽ/ህ ኃላፊነት ነው፡፡ ቀጣሪሽ/ህ የሚዘነጋ/የምትዘነጋ ቢሆን እንኳ ማስታወስ አለብሽ/ህ፡፡ ስራውን የቀለለ ለማድረግ በአባሪ 2 ላይ በተቀመጠው የቀን መቁጠሪያ ሰሌዳ ላይ ማስታወስ የሚገባሽ/ህን ዋና ዋና ቀናት ለምሳሌ ሰነዶችሽ/ህ የሚታደሱበትን ቀናት ጽፈሽ/ህ ያዢ/ዝ፡፡

የስራ ፈቃድ ‹ኢጃዜት አማል› በሊባኖስ ለአንድ ዓመት ለመስራት የሚያስችል ሕጋዊ ፈቃድ ሲሆን የሚሰጠው በሊባኖስ የሰራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፡፡ በየዓመቱም መታደስ አለበት፡፡:

የመኖሪያ ፈቃድ ‹ኢቃማ› የሚሰጠው በጠቅላይ ደህንነት ዳይሬክቶሬት ጀነራል ሲሆን እሱም በሊባኖስ ለአንድ ዓመት ሕጋዊ ሆኖ ለመኖር የሚያስችል ነው፡፡ በየዓመቱም መታደስ አለበት፡፡



**ይህን ታውቂ (ቅ) ኖሯል;**

- ፓስፖርትሽ/ህ አገልግሎት ዘመኑ ከማለቁ በፊት በየ 5 ዓመቱ መታደስ ይኖርበታል፡፡ የስራ ፈቃድሽ/ም/ የፓስፖርትሽ/ህ አገልግሎት ማብቂያው ከማለቁ ከ 7 ወር በፊት መታደስ አለበት፡፡ ስለሆነም በፓስፖርትሽ/ህ ላይ የተመለከተው የአገልግሎት ማብቂያው ከመድረሱ ከ 7 ወር በፊት የቀጣሪሽ/ህ/ን እርዳታ በመጠየቅ ወደ አገርሽ/ህ ኤምባሲ/ቆንሲላ በመሄድ ûep`fi/l/ን የማሳደስ ሂደትን መጀመር አለብሽ/ህ/፡፡

- ሊባኖስ በደረስሽ/ህ/ በ10 ቀናት ውስጥ የቀጣሪሽ/ህ/ን እርዳታ በመጠየቅ ለሠራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር የስራ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከት አለብሽ/ህ/፡፡

- የመኖሪያ ፈቃድ ሊባኖስ በገባሽ/ህ/ ከ3 ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ማግኘት አለብሽ/ህ/፡፡ ካልሆነ ግን ልትቀጪ/ጣ/ ትችያለሽ/ትችላለህ፡፡ ስለሆነም ሊባኖስ በገባሽ/ህ/ ከ 2 ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የመኖሪያ ፈቃድ መያዝ ይመረጣል፡፡

- የስራ ፈቃዱም ሆነ የመኖሪያ ፈቃዱ የሚገለግለው ለአንድ ዓመት ብቻ ስለሆነ የአገልግሎት ዘመኑ ከማለቁ በፊት መታደስ አለበት፡፡



## መታወቅ ያለባቸው ነጥቦች

- ዋናውን የስራ ውልሽ/ህ/ን ጨምሮ ፓስፖርትሽ/ህ/ንና ሌሎች ህጋዊ ሰነዶችሽ/ህ/ን በሙሉ የመያዝ መብት እንዳለሽ/ህ/ አትዘንጊ/ጋ/፡፡
- ቀጣሪሽ/ህ/ ፓስፖርትሽ/ህ/ን እንዲሁም የስራና የመኖሪያ ፈቃድሽ/ህ/ን ኮፒ ሊይዝ ይችላል፡፡
- ሐሰተኛ የግል ሰነዶች ከፍተኛ ችግር ሊያደርሱብሽ/ህ/ ከመቻላቸውም በላይ ለእስር ሊዳርጉሽ/ህ/ እንደሚችል ልትገነዘቢ/ብ/ ይገባል፡፡

## 3. ሊባኖስ ከደረስክ (ሽ) በኋላ የምታከናውኛ/ና/ቸው ዘጠኝ ነገሮች

1. ቤይሩት አየር ማረፊያ ትደርሻለሽ/ሳለህ::
2. ከደህንነት የመጡ እና ዩኒፎርም የለበሱ አንድ ወይም ከዚያ በላይ መኮንን/መኮንኖች ይቀበሉሻል/ሃል::
3. መኮንኖቹ ወደ ፓስፖርት ቁጥጥርና የሻንጣ መቀበያ ቦታ ይመሩሻ/ሃ/ል::
4. ሻንጣሽ/ህ/ን ከተቀበልሽ/ክ/ በኋላ በአየር ማረፊያው ወደ አንድ ክፍል ተወስደሽ/ህ ከአሰሪሽ/ህ ጋር ትገናኛለሽ/ህ/::
5. እንደደረስሽበት/ክበት ጊዜና የእለት ሁኔታ አንቺ/ተ/ና አሰሪሽ/ህ በቀጥታ ወደ አሰሪሽ/ህ ቤት አልያም ወደ አስቀጣሪው ኤጀንሲ ትሄዳላችሁ::
6. ከአዲሱ አሰሪሽ/ህ ጋር ሆናችሁ አካላዊና የተለያዩ የጤና ምርመራዎች ወደሚያደርግልሽ/ህ/ ሀኪም ዘንድ ትሄዳላችሁ::(ሰንጠረዥ 1 ይመልከቱ)
7. የስራ ቅጥር ውል ለመፈረም ወደ ውልና ማስረጃ ምዝገባ መስሪያ ቤት ትሄዳላችሁ::
8. ከዚያ አሰሪሽ/ህ ወደ ሰራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር የስራ ፍቃድሽ/ህ/ን ለማውጣት ይሄዳል::
9. ሊባኖስ በደረስሽ/ህ በ 3 ወራት ውስጥ ወደ ጠቅላይ ደህንነት መ/ቤት በመሄድ አሰሪሽ/ህ የመኖሪያ ፈቃድሽ/ህ/ን ማውጣት ይጠበቅበታል::

## 4. ከሊባኖስ መልቀቅ ስትፈልግ/ጊ

ከሊባኖስ ለቅቆ ለመውጣት የሚከተሉት ያስፈልጉሻ/ሃ/ል፡፡

1. ህጋዊ ፓስፖርት
2. ህጋዊ የመኖርያ ፈቃድ
3. ወደምትሄጂ/ድ/በት ሀገር የሚያደርስ የአየር ትኬት
4. የአሰሪሽ/ ማረጋገጫ

# ምዕራፍ ሁለት

# በሊባኖስ ዉስጥ እንደ ውጭ ዜጋ ያሉህ(ሽ) መብትና ግዴታዎች

## 1. የስራ ቅጥር ውልህ (ሽ) ምን ይላል ?

የውጪ ዜጋ የቤት ውስጥ ሠራተኛ እንደመሆንሽ መጠን የቅጥርና የስራ ሁኔታዎች አሰሪሽ/ህ (አንደኛው ተዋዋይ) እና አንተ/ቺ (ሁለተኛ ተዋዋይ)ጋር በውልና ማስረጃ ምዝገባ መ/ቤት ቀርባችሁ በምትፈራረሙት የቅጥር ውል ውስጥ ተብራርቶ ይገኛል፡፡የውሉ ሙሉ ቃል(ይዘት) በአባሪ 7 ውስጥ በራስሽ/ህ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ይገኛል፡፡

- **የስራው ዓይነት፡-** የተቀጠርሽ/ከ/ው ለቤት ሰራተኝነት ነው፡፡(የውሉ መግቢያ)
- **የስራው ቦታ፡-** የአሰሪሽ/ህ ቤት ነው፡፡(አንቀጽ 2)
- **የስራ ቅጥር ዘመን፡-** በአሰሪሽ/ህ በየዓመቱ መታደሱ እንደተጠበቀ ሆኖ 3 ዓመት ነው፡፡(አንቀጽ 4)
- **የስራ መጀመሪያ ቀን፡-** አንቺ/ተ እና ቀጣሪሽ/ህ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርባችሁ ውሉን የፈረማችሁበት ቀን ነው፡፡ ውሉ ለ 3 ወራት የሚቆይ የሙከራ ጊዜን ይጨምራል፡፡ (አንቀጽ 5)

ምንም ምክንያት ሳይኖረው አሰሪሽ/ህ ሌላ ሰው ቤት ሄደሽ/ህ እንድትሰሪ/ራ/ ወይም የቤት ሰራተኛ ሊሰራ ከሚገባው ውጪ የሆነ ሥራ እንድትሰሪ/ራ ቢጠይቅሽ/ህ በውሉ ያልተካተተ ስራ አልሰራም ብሎ መልስ የመስጠት መብት እንዳለሽ/ህ አትዘንጊ/ጋ፡፡ በአንጻሩም አንቺ/ተ/ም ለሌላ ሰው በመስራት የስራ ውልሽ/ህ/ን መተላለፍ የለብሽም፡፡

- **ወርሀዊ ደመወዝ**

1. በውሉ ላይ የተመለከተው የደመወዝ መጠን እንዲከፈልሽ/ህ መብት አለህ፡፡ እንዲሁም፡-

ደመወዝሽ/ህ በጥሬ ገንዘብ/ካሽ ሊከፈልሽ/ህ ወይም ባለሽ/ህ ሂሳብ ሊተላለፍልሽ/ህ ይችላል፡፡ በሁለቱም ሁኔታዎች አንቺ/ተ/ም ሆንሽ/ክ አሰሪው ደረሰኝ መፈረም ይኖርባችኋል፡፡ይህን አመቺ ለማድረግ የሚያስችል የደረሰኝ ደብተር በዚህ መመሪያ ውስጥ ተካቷል፡፡

2. ስራ በሰራሽ/ህ/በት በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ ሙሉውን ደመወዝሽ/ህ/ን ሳይዘገይ የማግኘት መብት አለሽ/ህ፡፡

- **የስራ አፈጻጸም ባህርይ**

በስራ ውሉ ላይ የተመለከቱትን የስራ ግዴታዎች በአግባቡ መወጣትና ለሥራሽ/ህ/ም ኃላፊነት መውሰድ አለብሽ/ህ/፡፡ በአሰሪሽ/ህ፤ በመኖሪያ ቤቱና ከመኖሪያ ቤቱ ውጪ በአንቺ/ተ እና በአሰሪሽ/ህ መካከል ችግር የሚፈጥሩ ባህርያትን ከማሳየትና ከመተግበር ተቆጠቢ/ብ/፡፡ (አንቀጽ 7)

የማታውቂያ/ቃ/ቸውን ሰዎች በቀላሉ በማመን ችግር ዉስጥ እንዳትወድቂ/ቅ ተጠንቀቅ/ቂ፡፡ የአሰሪሽ/ህ/ንና የቤተሰቡን የግል ህይወት አክብር/ሪ፡፡ከቤት ውጪ የግል ጉዳችን አትወያዩ፡፡የአሰሪሽ/ህን ሃይማኖት አክብር/ሪ፡፡አሰሪሽ/ህ/ም የአንቺ/ተ/ን ሃይማኖት የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

- **ጥቅማ ጥቅም**

1. በሚገባ እንድታርፊ/ፍ እና የግል ነጻነትሽ/ህ እንዲጠበቅ የሚያደርግ ንጹህ፤ደህንነቱ የተጠበቀና ጤናማ የማረፊያ ቦታ የማግኘት መብት አለሽ/ህ/፡፡

በራስሽ/ህ ገንዘብ የምትፈልጊ/ገ/ውን ልብስ ለመግዛት እንድትችይ/ል የሚፈቅዱ ቤተሰቦች አሉ፡፡በሌላ በኩል ዩኒፎርም ገዝተው እንድትለብሽ/ስ የሚፈልጉ አሰሪዎችም ይኖራሉ፡፡

2. ለአየሩ ጸባይ ተስማሚ የሆኑ ልብሶችን የማግኘት እንዲሁም ከፍላጎትሽ/ህ ጋር የተጣጣሙ በቂ ምግቦች በወቅቱ የማግኘት መብት አለሽ/ህ/፡፡(አንቀጽ 8)

- **ህክምና**

አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ የህክምና እርዳታ የማግኘት መብት አለሽ/ህ፡፡ ይህም ማለት ሀኪም ማየት በሚያስፈልግሽ/ህ ጊዜ ሁሉ አሰሪሽ/ህ ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ አሰሪሽ/ህ ከጥሩ የመድን(ኢንሹራንስ) ኩባንያ ጋር ግንኙነት በመፍጠርና በየዓመቱ ተገቢውና ክፍያ በመፈጸም የህክምና ወጪሽ/ህ/ን (በሆስፒታል መተኛትን ጨምሮ) በኢንሹራንስ እንዲሸፈን ማድረግ አለባ/በ/ት፡፡

የዓይንና የጥርስ ህክምናዎች ብዙ በህክምና ኢንሹራንስሽ/ህ ውስጥ ላይካተቱ ይችላሉ፡፡(አንቀጽ 9)

- **የስራና የመኖርያ ፈቃዶች**

ሊባኖስ ከደረስሽ/ህ በኋላ ወቅታዊ የስራና የመኖርያና የስራ ፈቃዱ እንዲኖርሽ/ህ እና በአሰሪሽ/ህ ወጪ በየአመቱ እንዲታደሱ ማድረግ የአሰሪሽ/ህ ኃላፊነት ነው፡፡(አንቀጽ 10) (ለተጨማሪ ማብራሪያ በምዕራፍ 1 ስር ያለውን ይመልከቱ)

- **የስራ ሰዐት**

በቀን ውስጥ ተከታታይ ሳይሆን በአማካይ ለ10 ሰዐታት የመስራት መብት ያለሽ/ህ ሲሆን ሌሊት ደግሞ የ 8 ሰአት ያልተቋረጠ እረፍት የማግኘት መብት አለሽ/ህ፡፡ (አንቀጽ 11)

- **ሳምንታዊ እረፍት**

ለ24 ያልተቋረጡ ሰዓታት የሚቆይ የአንድ ቀን እረፍት በየሳምንቱ የማግኘት መብት ያለሽ/ህ ሲሆን ለራስሽ/ህ ኃላፊነት የመውሰድ ግዴታ አለብሽ/ህ፡፡ ማረፍ የምትፈልጊ/ገ/ው በየትኛው እለት እንደሆነና በዚህ ቀን ምን መስራት እንደምትፈልጊ/ግ ከአሰሪሽ/ህጋር ተነጋግረሽ/ህ ልትስማሚ/ማ ይገባል፡፡(አንቀጽ 12)

- **የአመት እረፍት**

በአንድ አመት ውስጥ የ 6 ቀናት እረፍት ይኖሩሻል/ሃል፡፡ እነዚህን ቀኖች መጠቀም የምትፈልጊው/ገው መቼ እንደሆነና በእነዚህ ቀናት ምን መስራት እንደምትፈልጊ/ግ ከአሰሪሽ/ህጋር ልትነጋገሪ/ር ይገባል፡፡(አንቀጽ 12)

- **የመጓጓዣ ወጪዎች**

የስራ ውልሽ/ህ ሲያበቃ የመመለሻ የአየር ቲኬት የማግኘት መብት አለሽ/ህ፡፡ ነገር

ግን ከውል መቋረጥ ጋር በተያያዘ ይህን መብት የሚያስቀሩ ሁኔታዎች መኖራቸውን ‹የውል መቋረጥ› ከሚለው ክፍል ትረዳለሽ/ትረዳለህ፡፡ (አንቀጽ 13)

- **ከቤተሰብ ጋር ስለመገናኘት**

በስልክም ሆነ በሌላ የመገናኛ ዘዴ ከቤተሰቦችሽ/ህ ጋር የመገናኘት መብት አለሽ/ህ፡፡ አሰሪሽ/ህ ከቤተሰቦችሽ/ህ ጋር የምትገናኚበትን/በትን መንገድ የማመቻቸት ኃላፊነት ያለበ/ባ/ት ሲሆን በየወሩ አንድ የስልክ ጥሪ ሲሽፍን/ስትሽፍን አንቺ/ተ የተቀረውን ጥሪ መሽፈን ይኖርብ/ሀ/ል፡፡(አንቀጽ 14) (በምእራፍ 4.8 ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ)

- **የህመም ፍቃድ**

በስራሽ/ህ ምክንያት ህመም ወይም ጉዳት ከደረሰብህ/ሽ የወሩን አጋማሽ ለሆነ ጊዜ ከሙሉ ደመወዝ ጋር እንዲሁም ለቀሪው የወር አጋማሽ ከግማሽ ደመወዝ ጋር የተጣመረ እረፍት የማግኘት መብት አለሽ/ህ፡፡ ህመም መኖሩን የሀኪም ምስክር ወረቀት በማቅረብ ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡(አንቀጽ 15)

- **የስራ ውል መቋረጥ**

1. በአሰሪሽ/ህ ላይ ከባድ ጉዳት የሚያደርስ ድርጊት ከፈጸምሽ/ህ ወይም በሊባኖስ ህጎች መሰረት የሚያስቀጣ ድርጊት ከፈጸምሽ/ህ አሰሪሽ/ህ ከአንቺ/ተ ጋር ያለውን ውል ሊያቋርጥ/ልታቋርጥ ትችላለች/ይችላል፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ የመመለሻ ትኬትሽ/ህ/ን ወጪ የምትችይው ራስሽ/ህ ነሽ/ህ፡፡ (አንቀጽ 16)

2. ደመወዝ ባልተከፈለሽ/ህ ጊዜ ወይም ለ3 ተከታታይ ወራት ውሉ ከሚመለክተው ያነሰ ደመወዝ ከተከፈለሽ/ህ፤ በህክምና የምስክር ወረቀት የስነልቦና ወይም አካላዊ ጥቃት ከደረሰብሽ/ህ፤ የጉልበት ብዝበዛ ከተፈጸመብህ/ሽ እና እንደ ቤት ሠራተኛ

መስራት ከሚገባሽ/ህ ስራ ውጪ ለመስራት ከተገደድሽ/ህ ከአሰሪሽ/ህ ጋር ያለሽ/ህ/ን ውል ማቋረጥ ትችያለሽ/ትችላለህ፡፡ በእነዚህ ሁኔታዎች ውሉ ከተቋረጠ የመመለሻ ትኬት የመግዛት ኃላፊነት የአሰሪሽ/ህ ይሆናል፡፡(አንቀጽ 17)

- **አለመግባባቶች**

በስራ ቅጥር ውሉ ውስጥ ከተጠቀሱት መብቶችና ግዴታዎች ጋር በተያያዘ በአንቺ/ተ እና በአሰሪሽ/ህ መካከል አለመግባባት የተነሳ እንደሆነ አንቺ/ተ/ም ሆንሽ/ህ አሰሪሽ/ህ ችግሩ እንዲፈታ ለሠራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር አቤቱታ ማቅረብ ትችላላችሁ፡፡ (አንቀጽ 18) ችግሩ በዚህ ካልተፈታ ጉዳዩ ለሊባኖስ ፍ/ቤቶች ይተላለፋል፡፡(አንቀጽ 19)(ምእራፍ 3.2 ይመልከቱ)

- **ቅጂዎች**

የስራ ቅጥር ውሉ የአንተ/ቺ/ን ቋንቋ ጨምሮ በተለያዩ ቋንቋዎች በአራት ኮፒዎች ይዘጋጃል፡፡ ውሉን መፈረምሽን/ህን፤ መቀበልሽ/ህ/ን እና አንድ ኮፒ ለራስሽ/ህ ማስቀረትሽ/ህ/ን አረጋግጪ/ጥ፡፡

# ምዕራፍ 3

# ችግር በሚገጥምሽ(ህ) ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚገባሽ(ህ)

## 1. በሊባኖስ በሕጋዊ መንገድ ለመኖር የሚፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ካልተሟሉ ችግር ውስጥ ገብተሻል ማለት ነው፡፡

- **በሕጋዊ መንገድ የመኖር መብትን ሊያሳጡ የሚያበቁ ሁኔታዎች**



የሥራ ፈቃድ ቪዛሽ(ህ) ወይም የመኖሪያ ፍቃድሽ(ህ) የማደሻ ጊዜው ካለፈ፤

- ከአሰሪሽ/ህ ቤት ጠፍተሽ(ህ) ከሄድሽ(ክ) ድርጊቱ "ጠፍ(ቶ) የሄደ(ች)" በመባል ይታወቃል፡፡ እንዲሁም በሥራ ውሉ የተመለከተውን ሥራ ሕጋዊ ወይም አሳማኝ ምክንያት ሳይኖርሽ(ህ) ከተውሽ(ህ)፤
- በሕገወጥነት (ያለ ሥራ ፈቃድ)ሥራ የምትሰሪ(ራ) ከሆነ፡
- እንደስርቆት፣ ግድያ፣ ዝሙት አዳሪነት፣ ማጭበርበር፣ ሠነዶችን መሠረዝና መደለዝ፣ በሰው ላይ ጉዳት ማድረስ ወዘተ.... የመሳሰሉ የወንጀል ድርጊቶችን ስትፈፅሚ(ም)፡፡

- **በሕጋዊ መንገድ ለመኖር የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ሲጓደሉ ምን ይፈጠራል?**



**በሊባኖስ የመኖርና የመሥራት ፍቃድሽ(ህ)ን ታጫለሽ/ታጣለህ፡፡ በመሆኑም ሰዎች ባለሽ(ህ)በት አስጊና ሕገ ወጥ ሁኔታ ምክንያት አለአግባብ ሊጠቀሙብሽ(ህ) እና የጉልበት ብዝበዛ ሊያደርሱብሽ(ህ) ይችላሉ፡፡**

- በማስፈራራት የክፍያ ግዴታ ውስጥ እንድትገቢ(ባ) የሚያደርጉሽ(ህ) ሰዎች ሊያጋጥሙሽ(ህ) ይችላሉ። (የገንዘብ፣ አገልግሎት እና በባርነት ማገልገል) እንዲሁም አካላዊ፣ ወሲባዊና የመሳሰሉ ጥቃቶች ሊደርሱብሽ(ህ) ይችላሉ።

- እያዛለሁ፣ እታሰራለሁ፣ ወደ አገሬ ይመልሱኛል በሚል ስጋት ውስጥ ትኖሪያለሽ(ህ)።

- በሕጉ አግባብ ተይዘሽ(ህ) ታስረሽ ወደ አገርሽ(ህ) ልትላኪ(ክ) ትችያለሽ(ላለህ)፤ ምክንያቱም በሊባኖስ ሕግ ስፖንሰርሺፕ ሥርዓት መሰረት የሃገሪቱን የስደተኛ ጉዳይና የመኖሪያ ሕጎችን ጥሰሻ(ሀ)ልና ነው።

- ሕጋዊ ለሆኑ ሠራተኞች የሚሰጠውን የሕግ ከለላ፣ ሕክምናና ሌሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት ችግር ሊገጥምሽ(ህ) ይችላል።

- በሕገወጥ አቋምሽ(ህ) ምክንያት ተይዘሽ(ህ) ሥር ቤት እንድትገቢ(ባ) ከተደረገ ጉዳዩ "እልባት" እስከሚያገኝ ድረስ የሊባኖስ ባለስልጣናት በእስር ማቆያው ማዕከል ሊያቆዩሽ(ህ) ይችላሉ።

- እንደ ስርቆት፣ ዝሙት አዳሪነት፣ ወዘተ… ዓይነት ወንጀል መፈፀምሽ(ህ) ከተረጋገጠ የወንጀል ጉዳይ በሚያይ ፍርድ ቤት ፊት ቀርበሽ(ህ) የእስር ቅጣት ትቀበያለሽ (ትቀበላለህ)።

- በወንጀል ተፈርዶብሽ(ህ) እስር ቤት መግባት በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ለእስር ከሚዳርግ የወንጀል ተግባር ከመፈፀም ለመቆጠብ በጣም መጠንቀቅ አለብሽ(ህ)።



## ሠንጠረዥ 3. ጠፍቶ ስለመሄድ

- o በመጎሳቆል
- o ደመወዝ በመከልከል
- o በቋሚነት ከመቀጠር በነፃነት ተንቀሳቅሶ በመስራት የበለጠ ገንዘብ ለማግኘት በማሰብ
- o ሥራውን በመጥላት

ከአሰሪዋ(ው) ቤት ወጥ(ቶ) የሄደች(ው)ን የውጪ ዜጋ የቤት ሰራተኛ ሁኔታ ለመግለፅ ዘወትር የሚጠቀሙበት አባባል ነው::

**አስታውሺ(ስ)፡-**

- ❖ ከአሰሪሽ(ህ) ቤት ጠፍቶ መሄድ በፊት ከነበርሽ(ክ)በት የበለጠ ወደማይመች ወይም አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ሊያስገባሽ(ህ) ይችላል::
- ❖ ከአሰሪሽ(ህ) ቤት የመውጣቱን ነገር የመጀመሪያ ምርጫ አታድርጊ(ግ)::
- ❖ ችግርሽ(ህ) በተለይ በውሉ ላይ ከተመለከቱት መብቶችሽ ጋር የተያያዘ ከሆነ ችግሩን ለመፍታት ከአሰሪሽ(ህ) ጋር መወያየቱን የመጀመሪያ ምርጫ(ህ) አድርጊ(ገ)ው
- ❖ በዚህ መልክ መነጋገሩ አልሳካ ብሎ የአሰሪሽ(ህ)ን ቤት መልቀቅ ካስፈለገሽ(ህ) በዚህ መምሪያ አባሪ 2 ውስጥ "እርዳታ ስለመጠየቅ" በተሰኘው ርዕስ ስር የተዘረዘሩትን ሰዎች ካነጋገርሽ(ህ) በኋላ ብቻ መሆን አለበት::
- ❖ ያሉሽ(ህ) ምርጫዎች እና ውጤቶቻቸው

-የተሰጡሽ(ህ)ን ምክሮች

-ድርጊትሽ(ህ) የሚያስከትል ሁኔታ በግልፅ መረዳትሽ(ህ) ን እርግጠኛ ሁኚ(ን)::

## ጠቃሚ ጥቆማዎች

- አስቸጋሪ ሁኔታዎች በሚፈጠሩበት ወቅት፡-
  - “ተረጋጊ(ጋ)”
  - “አትደናገጪ(ጥ)”
  - “በጥድፊያና ተስፋ በቆረጠ መንፈስ ውስጥ ምንም ዓይነት ርምጃ አትውሰጂ(ድ)”
  - “ጊላ ሊቆጭሽ”(ህ) ስለሚችል፣ ርምጃዎችሽ(ህ) በቁጣና በፍርሃት ላይ የተመሰረቱ እንዳይሆኑ ተጠንቀቂ(ቅ)”
  - ችግር የማያስከትልና በጣም ተስማሚ የሆነ መፍትሔ ለማግኘት ትኩረት ስጪ(ጥ)፡፡
  - “በደህንነትሽ(ህ) ላይ አደጋ ሊያመጣ የሚችል ማናቸውንም ነገር ከመፈፀም ተቆጠቢ(ብ)”
  - “እርዳታ እንዲደረግልሽ(ህ) ጠይቂ(ቅ)፣ ከጎንሽ(ህ) የሚቆሙ እንዳሉ አስታውሺ(ስ)”
  - “ሊረዱሽ(ህ)የሚችሉ አሉ”
  - በቅድሚያ በዚህ መምሪያ ውስጥ “እርዳታ መጠየቅ” በተሰኘው ርዕስ ሥር የተሰጡትን የስልክ ቁጥሮች ለመደወልና እርዳታ ለማግኘት ሞክሪ(ር)፤ የአገርሽ(ህ)ን ኤምባሲ የእርዳታ ጥሪ መስመሮችን፤ የሠራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር የጠቅላላ ደህንነት ተቋም ወዘተ....)
  - ስለአለሽ(ህ)በት ሁኔታ በግልጽ፣ በሃቀኝነት አስረጂ(ዳ) እንዲሁም ስለሚሰጡሽ(ህ) አማራጮች በደንብ አድምጪ(ጥ)፡፡

- “ስልክ ማግኘት ካቃተሽ(ህ) ጠይቂ(ቅ) ወይም

  “ጎረቤቶችሽን እንዲረዱሽ(ህ)” ጠይቂ(ቅ)

  “አብሮሽ(ህ)ከሚሰራ እና ከምታምኚ(ነ)ው ሌላ ሰራተኛ እርዳታ

  ጠይቂ(ቅ)”፡፡

## 2. አለመግባባት ሲነሳ ምን ማድረግ እንደሚገባ

እንደ አንድ ሠራተኛ ከአሰሪሽ(ህ)ጋር የሰመረ ግነኙነት ይኖርሻ(ሀ)ል፡፡ የሚል ግምት አለን፡፡ ሆኖም ችግሮች ሁሌም ቢሆን ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ ባለመግባባት ወይም የምትፈልጉት ባለመሟላቱ በአንቺ(ተ) እና በአሰሪሽ(ህ) መካከል አንዳንድ ጊዜ አለመግባባት ሊነሳ ይችላሉ፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ አነስ ላሉት ችግሮች መፍትሔ ለማግኘት በቅድሚያ አሰሪሽ(ህ) ጋር በመግባባትና በግልፅ ለመወያየት ጥረት አድርጊ(ግ)፡፡

ከአሰሪሽ(ህ) ጋር መልካም ግንኙነት መኖሩ ጥሩ ሆኖ ሳለ፣ አንዳንድ ጊዜ የቋንቋ መለያየት እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡ ሃሳብሽ(ህ)ን በትክክል ለማስረዳት እንዲሁም አሰሪሽን(ህ) በትክክል ለማስረዳት እንዲሁም አሰሪሽ(ህ) የሚልሽ(ህ)ን በግልፅ ለመረዳት ሊያቅትሽ(ህ) ይችላል፡፡

ሌላው ጠቃሚ ነገር ዐረብኛ ማወቅ ነውና ሥራሽ(ህ) ቦታ ላይ ሆነሽ(ህ) የዐረብኛ ቋንቋ ለመማር ሞክሪ(ር)፡፡ ሊባኖስ ውስጥ በአንቺ(ተ) በፊት መጥተው የቆዩ የአገርሽ(ህ)ን ልጆች አንዳንድ ቃላት በማስተማር እንዲረዱሽ(ህ) ጠይቂ(ቅ)፡፡ ለዚሁ ሲባል በዐረብኛ ቋንቋ ውስጥ ያሉ ጥቂት መሰረታዊ የዐረብኛ ቃላት አቅርበንልሻ(ሀ)ል፡፡ ”አባሪ1 ላይ ስለዐረብኛ ቋንቋ የሰጠን ተመልከቺ(ት)” በተጨማሪም ለአሰሪሽ(ህ) ያለሽ(ህ)ን ሃሳብ ለመረዳት

በምትፈልጊ(ግ)በት ጊዜ በርጋታና በትዕግስት ለመነጋገር መሞከር እንዳለብሽ(ህ) እናሳስብሻ(ሀ)ለን።

## 3. በሥራ ላይ የሚደርስ ጥቃት ምድንነው?



ጥቃት ማለት አሰሪሽ(ህ) ወይም ማናቸውም የቤተሰቡ/ቧ አባል ያለአግባብ ሲበድሉሽ(ህ) (ሲያሰቃዩሽ(ህ)) ነው። ጥቃት ሲደርስ ለጠቅላይ ደህንነት ተቋም በ 48 ሰዓት ውስጥ ሪፖርት መደረግ አለበት።

የተለያዩ የጥቃት አይነቶች አሉ።

1. **የኢኮኖሚ ጥቃት:-** ይህ ማለት የገባሽ(ኸ)ው የሥራ ቅጥር ውል፤ የቅጥር ሁኔታ ወይም የስራ ሁኔታ በአሰሪሽ(ህ) ሲጣስ ሲሆን፣ የደሞዝሽ(ህ) በወቅቱ አለመከፈል፣ ተቀንሶ መከፈል፣ ደሞዝሽ(ህ)ን ጭራሹኑ መከልከል፣ ሕክምና የማታገኚ ከሆነ፣ በቂ መኖሪያ ቦታ፣ ምግብ አለማግኘት....ወዘተን ያጠቃልላል።

2. **የስነልቦና ጥቃት:-** ቀጣሪሽ(ህ) ከቤተሰቦችሽ(ህ) ጋር ለመገናኘት ሲከለክልሽ(ህ) (ስትከለክልሽ)፤ እንደልብ እንዳትንቀሳቀሽ(ስ)ና ትርፍ ጊዜ እንዳይኖርሽ(ህ)፣ አንድ ክፍል ውስጥ ሲዘጋብሽ(ህ) ስትዘጋብሽ(ህ) ወይም ከቤት እንዳትወጪ(ጣ) ሲከለክልሽ(ህ)፣ ስትከለክልሽ(ህ) ወዘተ....።

3. **የቃል ጥቃት:-** ክብረ-ነክ ቃላት፣ ስድብ፣ ማሳፈር፣ ንቀት፣ በዘርሽ(ህ)፣ በሃይማኖትሽ(ህ)፣ በግል የአናናር ዘይቤሽ(ህ)፣ በግል ጠባይሽ(ህ) ወዘተ..... መሳለቅ።

4. **አካላዊ ጥቃት:-** መደብደብ፤ መቆንጠጥ፤ በርግጫ መምታት፤ ማቃጠል፤ ወዘተ……(ዝርዝሩ ብዙ ነው)

5. **ወሲባዊ ጥቃት** :- ከቤተሰቡ አባላት በአንዱ ያለፈቃድሽ(ህ) ወሲባዊ ግንኙነት እንድትፈፅሚ(ም) ስትገደጂ(ድ) ወይም አንድ ሰው የወሲብ ግንኙነት የመሳሰሉ ተግባራት ሲፈፀምብሽ(ህ)፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጥቃቶች ሲደርሱብሽ(ህ) የሥራ ውልሽ(ህ)ን ለማቋረጥ በቂ ምክንያት አለሽ(ህ)፡፡



*** አሠሪሽ(ህ)ን ወይም የርሱ(ሷ)ን ቤተሰቦች ማመናጨቅና ያለአግባብ መረበሽ እንደጥቃት እንደሚቆጠር፣ በመሆኑም አሰሪሽ(ህ) በዚህ ላይ ተመርኩዞ የኮንትራቱን ውል ለማፍረስ በቂ ምክንያት እንዳለው(እንዳላት) አትዘንጊ(ጋ)፡፡ እንደፈፀምሽ(ከ)ው የጥቃት አይነት በሊባኖስ ሕግ መሰረት ልትከሰሺ(ስ) ና ልትቀጪ(ጣ) ትችያለሽ(ህ)፡፡**

## 4. <u>አሰሪን ስለመቀየር</u>

ከአዲሱ ሥራና ከመኖሪያው ሁኔታ ጋር እስክትለማመጂ(ድ) ድረስ የመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራት በጣም ከባድ ሊሆኑብሽ(ህ) ይችላሉ፡፡ በሥራው ላትደሰቺ(ት) ትችያለሽ (ትችላለህ)፡፡ ሥራው አስቸጋሪ፣ ከባድና አድካሚ እንዲሁም ረጅም ጊዜ የሚወስዱ ሊሆን ይችላል፡፡ ብቸኝነት፣ ማንም ያልተረዳሽ(ህ) ወይም የበደሉሽ(ህ) ሆኖ ሊሰማሽ(ህ) ይችላል፡፡

- ከበድ ያለ እርምጃ ከመውሰድሽ(ህ) በፊትና አሰሪሽ(ህ)ን (ሥራሽ(ህ)ን ከመቀየርሽ(ህ) በፊት በቅድሚያ በእነዚህ ችግሮች ቅሬታዎች እንዲሁም ምቾት የማጣት ሁኔታ ላይ ከአሰሪሽ(ህ) ጋር መወያየትና ለቅሬታዎችሽ(ህ) መፍትሔ ስለሚገኝበት መንገድ መሻት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡
- በዚህ መንገድ ያለሽበት ሁኔታ ለማሻሻል መፍትሔ ማግኘት ካልቻልሽ(ክ) አሰሪሽ(ህ)ን ወይም ሥራሽ(ህ)ን ለመቀየር እንዲቻል ጥያቄ ማቅረብ ትችያለሽ(ላለህ)፡፡ ሊባኖስ ከገባሽ(ህ)በት ጊዜ አንስቶ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራት ውስጥ በሊባኖስ የሚገኙ አስቀጣሪ ኤጀንሲዎች አንቺ(ተ)ንና አሰሪሽ(ህ)ን ሥራ(አሰሪ) ለመቀየር እንድትችይ(ል) የመርዳት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ከሦስት ወራት በኋላ ግን የጠቅላይ ደህንነት ተቋሙ በዚህ ጉዳይ ላይ ሊረዳሽ/ህ ይችላል፡፡

## 5. <u>የሕግ አገልግሎት ድጋፍ</u>

የሕግ አገልግሎት ድጋፍ ማግኘት መብት አለሽ/ህ፡፡ ማናቸውንም አለመግባባትን በሕግ የመፍታት ሂደት (የሕግ ክርክር) አንቺ(ተ)ን ወክሎ ፍርድ ቤት የሚቆምልሽ (ህ) ጠበቃ ሊመደብልሽ(ህ) ይችላል፡፡ የሕግ አገልግሎት ድጋፍ ማግኘት ከፍተኛ የገንዘብ ክፍያ የሚጠይቅ ስለሆነ ጠበቃ ለማነጋገርና እርዳታ እንዲሰጥሽ(ህ) ለማድረግ በቂ የገንዘብ አቅም ላይኖርሽ(ህ) ይችላል፡፡ የሆነው ሆኖ በአባሪ 2 ላይ እንደተመለከተው ነፃ የሕግ ድጋፍ ሊሰጡሽ(ህ) የሚችሉ አያሌ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይኖራሉ፡፡ ከአሰሪሽ(ህ) ጋር በማናቸውም ክርክር ፍርድ ቤት የምትቀርቢ(ብ)በት ሁኔታ ከተፈጠረ አስተርጓሚ እንዲያመጣልሽ(ህ) መጠየቅ የምትችይ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ የአገርሽ(ህ) ኤምባሲና ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በዚህ ረገድ ሊረዱሽ/ህ ይችላሉ፡፡ ከዚህም ሌላ

የአገርሽ(ህ)ን ኤምባሲ ወይም ቆንሲል በሕግ አገልግሎትም ሆነ በማስተርጎም ሥራ እንዲረዱሽ(ህ) የመጠየቅ መብት አለሽ(ህ)፡፡



**ጠቃሚ ጥቆማዎች**

- በአንቺ(ተ) በአሰሪሽ(ህ) መካከል በአስቸኳይ መፈታት ያለበት ከባድ አለመግባባት ወይም ችግር ከተፈጠረ ወዲያውኑ ስልክ ለመደወል እንድትችይ(ል) በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ቁጥሮች በአዕምሮሽ(ህ) መያዝ አለብሽ(ህ)፡፡
- በመኖሪያሽ(ህ) ወይም በአካባቢሽ(ህ) ድንገተኛ አደጋ ቢፈጠር ማለት ፖሊስ ወይም አንቡላንስ እንዲደርስልሽ(ህ) ለማድረግ የሚያችልሽ(ህ) መረጃ በዝርዝሩ ውስጥ ተካትቷል፡፡

## 6. <u>ተጨማሪ መረጃዎች</u>

➢ **በሥራ ቦታ ላይ ደህንነትን ስለመጠበቅ**

- ክሎሪንን ከሙቅ ውሃ ጋር ላለመጠቀም ተጠንቀቂ(ቅ)፡፡ ለጽዳት ኬሚካሎችን የምትጠቀሚ(ም) ከሆነ ከፕላስቲክ የተሰሩ ጓንቶች ማድረግ አለብሽ(ህ)፡፡ በፅዳት ሥራው ወቅት ኬሚካሎቹን በትንፋሽ ላለመሳብ ጭምብል ማጥለቅ የምትችይ(ል) ሲሆን እርጥብ በሆኑ መሬቶች ላይ ከመንሸራተት ለመዳን ተስማሚ ጫማዎችን ማድረግ ይኖርብሻ(ሀ)ል፡፡
- መስኮቶችን ወይም ሰገነቶችን እንድታፀጂ(ዳ) ከተጠየቅሽ(ህ) ስትጎነበሺ(ስ) ወይም መደገፊያዎቹን አሳልፈሽ(ህ) ለመድረስ ስትሞክሪ(ር) ሚዛንሽ(ህ) እንዳትስቺ(ት) ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብሽ(ህ) አትዘንጊ(ጋ)፡፡

- እርጥብ ልብሶች ለብሰሽ(ህ) ብዙ አትቆይ ( በዚህ ምክንያት ) ደረቅ ልብሶችን ቶሎ ለመቀየር ሞክሪ(ር)፡፡
- የአሰሪሽ(ህ)ን ትዕዛዞችና ጥያቄዎች ካልተረዳሽ(ህ) ደግመሽ(ህ) ከመጠየቅ አትቆጠቢ(ህ)፡፡

## ➢ ስለ ጋብቻ

- የውጪ ዜጋ ሠራተኛ ሆነሽ(ህ) በሊባኖስ ውስጥ እየሰራሽ(ህ) ጋብቻ መፈፀም ከፈለግሽ(ህ) ወይም (ለሴት ለማርገዝ እቅድ ካለሽ) የሚያስከትለውን የሕግ ውጤት ጠንቅቀሽ(ህ) ማወቅ አለብሽ(ህ) ::

- በሊባኖስ የሲቪል ጋብቻን የሚመለከት ሥርዓት (ደንብ) የለም፣ ሆኖም የሊባኖስ መንግሥት ከሀገሩ ውጪ ለተፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና ይሰጣል::
- በሊባኖስ ሕገ መንግሥት መሰረት ማንም ሰው ጋብቻ ቢፈፅም ሕጋዊ ነው፣ ሆኖም በአንድ የካፊል (ስፖንሰርሺፕ) ቪዛ መብት ብቻ ያለው የውጭ ዜጋ ሰራተኛ እና በሊባኖስ ዜጋ መካከል የሚፈፀም ጋብቻ አስቸጋሪና የተወሳሰበ ነው:: የካፊል ቪዛ መብት ብቻ ያላቸውና ጋብቻ ለመፈጸም ጥያቄ ያላቸው የውጪ አገር ዜጋ ሠራተኛ ምክር ለማግኘት የራሳቸውን አገር ኤምባሲ እንዲጠይቁ ይመከራሉ፡፡ (አባሪ 2 ላይ “እርዳታ ስለመጠየቅ” የሚለውን ይመልከቱ)

## ➢ ስለ እርግዝና

- (ለሴት ሠራተኞች) ወደ ሊባኖስ ከመጓዝሽ በፊትና እዚያ ከደረስሽም በኋላ የእርግዝና ምርመራ እንድታደርጊ ትጠየቂያለሽ::

- በሊባኖስ በተለይ ሴት ስደተኛ የቤት ሰራተኞችን የሚመለከት በሥራ ላይ የዋለ ለእርግዝና የሚሸፈን የኢንሹራንስ ፖሊሲ የለም::
- አርግዘሽ ከተገኘሽ በሃገሪቱ ውስጥ መቆየት አትችይም፣ ስለዚህ የአስቀጣሪው ድርጅት በመጀመሪያዎቹ ሦስት ወር የኮንትራት ጊዜያት ወደ አገርሽ ይመልስሻል፡፡
- ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ ጥረት የተደረገ ቢሆንም፣ በወቅቱ ያለውን ሁኔታ መገንዘብ አለብሽ፡፡
- ለስደተኛ የቤት ሰራተኞች የሚገባው የጤና ኢንሹራንስ የማዋለጃ ገንዘብን የማይጨምር ከመሆኑም ባሻገር የሥራ ውልሽም ቢሆን የወሊድ ፈቃድን አያካትትም፡፡
- ሀሰተኛ የእርግዝና ምርመራ ውጤት በማቅረብ ለማታለል መሞከር አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሊያስገባሽ ይችላል::
- በሊባኖስ ሕግ መሠረት አንዲት ሴት ያላትን ዜግነት ለልጆቿ ለማስተላለፍ አትችልም፡፡

- **"በሰዎች መነገድ"**

- ሰዎችን በሕገወጥ መንገድ የማስተላለፍ ሁኔታዎችን ለማወቅ በሠራተኛ ፍልሰት (በሠራተኞች ከአገር ወደ አገር መዘዋወርና ሰዎችን በሕገወጥ መንገድ ከአንዱ አገር ወደሌላው ማስተላለፍ ያላቸውን ልዩነት በሚገባ ማወቅ አለብሽ(ህ)::
- ሰዎችን በሕገወጥ መንገድ ከአንዱ አገር ወደ ሌላው የማስተላለፍ ተግባር ሲፈፀም፣ በአባሪ 2 ውስጥ ያሉት የስልክ ቁጥሮች በመደወል ማስታወቅ ያስፈልጋል፡፡

“ሰዎችን በሕገወጥ መንገድ ከአንዱ አገር ወደሌላው ማስተላለፍ” ማለት ሰዎችን መመልመል፣ ማጓጓዝ፣ ከአገር አስወጥቶ ወደሌላ መውሰድ፣ ማቆየት ወይም መቀበል፣ በማስፈራራት ወይም በሌሎች የማስገደጃ ዘዴዎችን በመጠቀም፣ መጥለፍ፣ ማጭበርበር፣ ማታለል፣ ሥልጣንን ያለአግባብ በመጠቀም ወይም አንድን ሰው ለመበዝበዝ ሲባል፣ በክፍያ ገንዘብ መስጠት ወይም መቀበል ማለት ነው::

“ብዝበዛ” ሲባል ዝሙት አዳሪነት፣ ወይም ሌላ ወሲባዊ ብዝበዛን ማካሄድ፣ አስገድዶ ማሰራት ወይም አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣ ባርነት ወይም ከባርነት የማያንሱ ተግባራትን መፈፀም፣ ራስን ለሌላ ሰው ማሳደር ወይም ዋና ዋና የሰውነት አካላት ብልቶችን ማስወገድን ያጠቃልላል::

* የተባበሩት መንግሥታት የፖሌርሞ ፕሮቶኮል እ.ኤ.አ. 2000

# ምዕራፍ 4

# የሊባኖስን ባህል መለማመድ

**በስደት የመጣሽ(ህ) ሠራተኛ እንደመሆንሽ(ህ) እና የአሰሪሽን(ህ)ን ቤተሰቦች እንዲሁም የአገሩን ባህልና ልማድ በደንብ ማወቅ እና መለማመድ የአለመግባባት ችግር እንዳይኖር የሚረዳሽ(ህ) ሲሆን በሊባኖስ ያለሽ(ህ)ን ሕይወትና ሥራ ያሻሽለዋል::**

## 1. ስለሊባኖስ፡- ስለ አገሩ ሁኔታ መግለጫ



- ሊባኖስ በሜዲትራኒያን ባህር ምሥራቃዊ ጠረፍ ላይ ትገኛለች::
- ሊባኖስ ተራራማ አገር ናት፣ ይሁን እንጂ የአገሪቱ አንዳንድ ክፍሎች ሜዳማና ረጅም የባህር ጠረፍ ያላቸው ናቸው::
- ሊባኖስ 4 ሚሊዮን ያህል የሕዝብ ብዛት አላት::
- ከቤይሩት ቀጥሎ ዋና ዋና ከተሞች በአልቤክ፣ በትራውን፣ ቤይተዲን፣ ጃዚን፣ ጅቤይል፣ ጃውኒየህ፣ ሲዶን፣ ትሪፓሊ፣ የርና ዛሕል ናቸው:: ከሕዝቡ ገሚሱ ያህል የሚኖርባት ዋና ከተማ ቤይሩት ናት::
- የሊባኖስ ብሔራዊ ገንዘን ሊራ ይባላል። 1 የአሜሪካን ዶላር በ 1,500 ሊራ ይመነዘራል (ምንዛሪው ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊቀያየር ይችላል::) የአሜሪካን ዶላር እለት በእለት በሚካሄድ የንግድ ልውውጥ ይሰራበታል።




- የሊባኖስ የአየር ጠባይ ከቦታ የሚለያይ ሲሆን በመለስተኛ ሙቀትና በመለስተኛ ብርድ መካከል ይዋዥቃል፡፡ የሙቀቱ ወቅት ከሰኔ እስከ መስከረም የሚቆይ ሲሆን፣ ቀዝቃዛውና ዝናባማው ወቅት ከጥቅምት እስከ ሚያዚያ ይዘልቃል፡፡
- በሚያዚያና በግንቦት የሙቀቱ መጠን መካከለኛ ነው፡፡ የባህሩ ዳርቻ ምንጊዜም ከተራራው አካባቢ ይበልጥ ይሞቃል፡፡
- ለሞቃት ወቅት ከጥጥና ሌላ ቀለል ካሉ ጨርቆች የተሰሩ የበጋ ልብሶች ያስፈልጉሻ(ሀ)ል፡፡

- ለቅዝቃዜ ወቅት ወፍራም ጃኬት፣ የሚሞቅ ካልሲ፣ ሽፍን ጫማ፣ ስካርፍ (የአንገት ልብስ) እና ባርኔጣ ሊያስፈልግሽ ይቻላል፡፡

- በሊባኖስ የሚኖሩና የሚሰሩ የተለያየ ሃይማኖት ያላቸው፣ የተለያዩ ብሔርና ብሔረሰብ የሆኑ ሕዝቦች አሉ፡፡

- እነዚህ የተለያዩ ሕዝቦች በአንድ ላይ እንዲኖሩ የግድ የሃይማኖት፣ የጎሣና የዘር ልዩነቶችን አቻችሎ መኖር ያስፈልጋቸዋል፡፡ እነዚህን ልዩነቶች ማክበርና መቀበል አለባቸው፡፡

- በሃገሪቱ ውስጥ ያለው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ሁኔታ አንዳንድ ጊዜ ያልተረጋጋ የሚሆንበት ጊዜ አለ፣ ይህም በግል ደህንነትሽ(ህ) ላይ አንዳንድ ችግር ሊያከትልብሽ(ህ) ይችላል፡፡ በአገሪቱ ውስጥ የሚካሄደውን የፖለቲካ ሁኔታ ሁሉ መከታተልና አንዳንድ መሰረታዊ የሆኑ የደህንነት ጥበቃ ደንቦችን ማክበር አለብሽ/ህ፡፡ ለምሳሌ፡-ውጥረት በሚፈጠርበት ጊዜ ወዲያ ወዲህ ከማለት መቆጠብና ሰው ከተሰበሰበበት ቦታ ዘወር ማለት ያስፈልጋል፡፡

## 2. ባህላዊ ክንውኖች

- በሊባኖስ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ጮክ ብለው ይናገራሉ፣ ሆኖም ይህ ማለት ተቆጥተዋል ወይም አንቺ(ተ)ን ጠልተውሽ(ህ) ነው ማለት አይደለም፡፡ አንቺ(ተ) ካልለመድሽ(ከ)ው በተለየ መንገድ መናገራቸው ብቻ ነው፡፡

- ብዙ ሰዎች በአንድ ጊዜ እኩል ሊናገሩ ይችላሉ፡፡ ከተለያዩ የቤተሰብ አባላትም የተለያዩ ትዕዛዞችን ልትቀበይ(ል) ትችያለሽ(ላለህ)፡፡ እንደዚህ በሚሆንበት ጊዜ አሰሪሽ(ህ)ን በቅድሚያ የትኛውን መፈፀም እንዳለብ(ህ) በትህትና መጠየቅ አለብሽ(ህ)፡፡

- የሊባኖስ ሰዎች “አይሆንም” ለማለት የዐይን ሽፋላቸውን ከፍ በማድረግ፣ ራሳቸውን ወደ ጎንና ጎን በማነቃነቅ ወይም ራሳቸውን ቀና በማድረግ ሊገልፁ ይችላሉ፡፡
- የሊባኖስ ሰዎች በቤታቸው ውስጥ ብዙ እንግዶችን ጠርተው እስከ ሌሊት ድረስ መጋበዝ የተለመደ ነው፡፡

## 3. ከቀጣሪሽ(ህ) ቤተሰብ ጋር መዋሃድ

- ከቀጣሪሽ(ህ) ቤተሰብ ጋር ራስሽን(ህ)ን በደንብ ማዋሃድ አለብሽ(ህ)፡፡ ከቤተሰቡ ኑሮ ሕይወት ጋር ተጣጥሞ ለመኖር የአሰሪሽ(ህ)ን ማህበራዊ፣ ባሕላዊና ሃይማኖታዊ ልምዶችን እንደዚሁም የቤት ውስጥ ደንቦች /የሚዘወተሩ ድርጊቶችን ለመረዳት መሞከር አለብሽ(ህ)

## 4.ሃይማኖት

- ሊባኖስ እንደ ውጪ ዜጋ የቤት ውስጥ ሰራተኞች ለአንቺ(ተ)ም ጭምር የሚያገለግል ሕገ መንግሥት አላት፡፡
- ሃይማኖት በሊባኖስ ዋነኛ ነገር ነው፡፡ በየሥራቸው ብዙ አይነት ክፍሎች ያሏቸው ሁለት ዋና ዋና ሃይማኖቶች አሉ፡፡
- በሊባኖስ የሚገኙ የክርስቲያን ቡድኖችን/ንዑስ ክፍሎችን ብንወስድ፣ ካቶሊኮች፣ ማሮናይቶች፣ የግሪክ ኦርቶዶክሶች፣ ፕሮቴስታንቶችና ሌሎች ንዑስ ክፍሎችን ያጠቃልላሉ፡፡
- የሙስሊም ቡድኖች/ንዑስ ክፍሎች ሺአይቶችን፣ ሱኒዎችን፣ አላዊቴዎችን ወይም ድሩዜዎችን ያጠቃልላል፡፡

- እያንዳንዱ ሃይማኖታዊ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ የተለያየ የጋብቻ፣ የውርስ ወዘተ.... ደንቦች፣ ልማዶች እና የቤተሰብ ሕጎች አሉት፡፡
- የአሰሪሽ(ህ) ሃይማኖት ከአንቺ(ተ) ሃይማኖት ሊለያይ ይችላል፡፡ አንቺ(ተ)ና አሰሪሽ(ህ) አንዳችሁ የሌላችሁን ሃይማኖታዊ ተግባራት መረዳትና ማክበር አስፈላጊ ነው፡፡

## 5. ማህበራዊ ግብረገብነትና ባህርይ

በአንቺ(ተ) አገር ልምድ መሰረት ጥሩ ጠባይና ግብረገብነት ነው ተብሎ የሚታሰበው ነገር በሊባኖስ የሚገኘው (የምትገኘው) አሰሪሽ(ህ) ከሚያሳያቸው (ከምታሳያቸው) ባህሪያት የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ከአሰሪሽ(ህ) መነጋገሩ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

- አንቺ(ተ) እና አሰሪሽ(ህ) በውጪና በቤት ውስጥ እንዴት መልበስ እንዳለብሽ(ህ) መነጋገር ይኖርባችኋል፡፡ አንዳንድ ቤተሰብ ውስጥ አሰሪው የሚሰጠውን የሥራ ልብስ መልበስ የተለመደ ነው፡፡ በሥራ ላይ ያሉ ቁምጣ ወይም አጫጭር ቀሚሶችን፣ ሰውነትን የሚወጣጥሩ ሽሚዞችንና ልብሶችን መልበስ ነውር ነው፡፡
- (ለሴቶች) ወንዶችን በምታነጋግሩበት ጊዜ በባህል ልዩነቶች ምክንያት ያለመግባባት ሊፈጠር ይችላል፡፡ በአንቺ በኩል ምንም ጉዳት የሌለው የወዳጅነት አቀራረብ ነው ብለሽ የገመትሽው አኳኋን በሌላ ጠንከር ባለ ግንኙነት ውስጥ ለመግባት ፍላጎት ማሳየትሽ እንደሆነ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ያለመግባባት እንዳይፈጠር ለማድረግ በሊባኖስ ውስጥ ወንዶች ሴቶችን እንዴት እንደሚያነጋግሩ እና ለየሁኔታው ተገቢ የሆነ የአነጋገር ዘይቤ መኖሩን በሚገባ መርምሪ፡፡

## 6. ምግብ

በሊባኖስ የሚዘወተረው ምግብ የተመጣጠነና ለጤና ተስማሚ ነው፡፡ ብዛት ያለው ፍራፍሬን፣ አትክልት፡ ትኩስ አሣና ከባህር የሚገኙ ምግቦችን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ከእንስሳት የሚገኝ ቅባት እምብዛም አይበላም፡፡ ከሊባኖስ ልዩ ምግቦች በተለይ ታዋቂ የሆነው "ሜዜ" ተብሎ የሚጠራው ሲሆን፣ የወይራ ፍሬ፣ የፈረንጅ አይብ፣ እርጎ፣ ቋሊማ፣ አትክልትና ባለ አበባ ዕፅዋት፣ ሰላጣ ወዘተ.... የያዘ የምግብ ፍላጎት የሚያሰፋ ምግብ ነው፡፡



በተለያዩ ባህሎች የተለያዩ የምግብ ልምዶችና ባህሎች አሉ፡፡ ለምሳሌ በአንዳንድ ቤተሰቦች የአሳማ ሥጋ ካለመብላታቸውም በላይ የአሣማ ሥጋ ነክ የሆኑ ምግቦች በቤታቸው እንዲገባ አይፈልጉም፡፡ በሌሎች ቤተሰቦች ደግሞ በእጅ እየቆረሱ መብላት ነውር ሊመስል ይችላል፡፡ በአንዳንድ ቤተሰቦች የአልኮል መጠጥ ክልክል ነው፡፡

በመሆኑም፣ አንዳንድ የምግብ አይነቶችን መግዛትንና መመገብም በተመለከተ የቤተሰብ ደንብ እንዳለና እንደሌለ አሰሪሽን(ህ)ን መጠየቅ አለብሽ(ህ)፡፡

ያሉሽ(ህ)ን የምግብ ልምዶች በተመለከተ አሰሪሽ(ህ)ን ብታነጋግሪ(ር) አለመግባባት እንዲቀር እና አንዳችሁ የሌላችሁን የምግብ ፍላጎት ምርጫ እንድታከብሩ ይረዳል፡፡

## 7. የፅዳት ሁኔታ ደረጃ

- "ንፅህና" እንደቤቱ እንዲሁም ከአንዱ ባህል ወደ ሌላ ባህል ይለያያል፡፡
- አንቺ(ተ)ና አሰሪሽ(ህ) በአንድ ጣራ ሥር ስለምትሠሩና ስለምትኖሩ በፅዳት ዙሪያ ምን እንደሚጠብቅሽ(ህ) እንዲሁም ስለፅዳት ሁኔታ ደንቦች እንዳሉ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡
- የንፅህና ደረጃ ልዩነቶች በምግብ፣ በሣህን፣ በወለልና መስኮት ፅዳት እንደዚሁም የግል ሰውነት ፅዳት ሁኔታ ላይ ይንፀባረቃል፡፡
- ምግብና መጠጥ የምታስናዷ(ዳ)በትን የአሰራር ልምድ በአሰሪሽ(ህ) ፍላጎት ሁኔታ ማስተካከል ያስፈልግሻ(ሀ)ል፡፡
- በተለይ ህፃናት ልጆችን በምትንከባከቢ(ብ)በት ጊዜ የግል ንፅህናን መጠበቅ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ጉንፋን እንዳታስይዣ(ዛ)ቸው፣ እጆችሽ(ህ)ን በየጊዜው መታጠብ አለብሽ(ህ)፡፡

## 8. አገር ቤት ካሉ ዘመዶችሽ(ህ) ጋር እንዴት መገናኘት እንደሚቻል

**ለመገናኘት የሚያስፈልጉ መንገዶች ክፍያ በየጊዜው ይጨምራል ተብሎ ይታሰባል፣ ስለዚህ የዋጋ ጥማሪ እንዳለና እንደሌለ በየጊዜው መጠየቅ አለብሽ(ህ)፡፡**

- ሊባኖስ በቀጥታ መስመር ስልክ ሥርዓት ትጠቀማለች፡፡ የስልክ ካርድ በመጠቀም የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ የስልክ ጥሪ ለማድረግ የሚያስችሉ የስልክ መደወያ ቤቶች ይገኛሉ፡፡ በእነዚህ የስልክ መደወያ ቤቶች ያሉትን ስልኮች ለመጠቀም "ቴሌ ካርድ" የሚባል የስልክ ካርድ ከሱቅ መግዛት

ትችያለሽ(ለህ)፡፡ የመንግሥት ስልክ ቤቶች (በዐረብኛ "ሴንትራሌ" ይባላሉ) በመሄድ የአገር ውስጥና የውጪ አገር ስልክ ጥሪ አድርገሽ(ህ) ደውለሽ(ህ) በጥሬ ገንዘብ መክፈል ትችያለሽ(ላለህ)፡፡

- ስለ ፓስታ ቴምብሮችና ሌሎች የመልዕክት አማራጮችና አገልግሎቶች የሊባኖስ የሀገር ውስጥና የዓለም አቀፍ ፓስታ አገልግሎት ድርጅት ወደሆነው ሊባን ፖስት በመሄድ መጠየቅ ትችያለሽ(ህ)፡፡

## ሠንጠረዥ 4

**የዓለም አቀፍ ጥሪ የመጀመሪያ ቁጥሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡**

የምንፈልገውን የስልክ ቁጥሮች ከመጫናችን (ከመደወላችን) በፊት እነዚህን ቁጥሮች መጫን (መደወል)ቀጥሎም የምንፈልገውን ቁጥር ማስከተል ያስፈልጋል፡፡

| | |
|---|---|
| ባንግላዲሽ | 00880፤<br>ዳካ ለመደወል ፡ 00880-2 እና የስልክ ቁጥሩን |
| ኤርትራ | 00291፤<br>አስመራ ለመደውል ፡ 00291-1 እና የስልክ ቁጥሩን |
| ኢትዮጵያ | 00251፤<br>አዲስ አባበ ለመደወል ፡ 00251-1- እና የስልክ ቁጥሩን |
| ሕንድ | 0091፤<br>ዴልሂ ለመደወል ፡ 0091-11- እና ስልክ ቁጥሩን |
| ማዳጋስካር | 00261፤<br>አንታናና ሪቮ ለመደወል ፡ 00261-2- እና የስልከ ቁጥሩን |
| ፊሊፒንስ | 0063፤<br>ማኒላ ለመደወል: 0063-2- እና የስልክ ቁጥሩን |
| ሱዳን | 00249<br>ካርቱም ለመደወል 00249-11 እና የስልክ ቁጥሩን |
| ስሪላንካ | 0094፤<br>ኮሎምቦ ለመደወል ፡ 0094-1- እና የስልክ ቁጥሩን |

## 9. ገንዘብ ወደ አገር ቤት እንዴት እንደሚላክ

- ሊባኖስ እያለሽ(ህ) በዓለም አቀፍ የገንዘብ መላኪያ አገልግሎት ድርጅቶች አማካይነት ገንዘብ ወደ አገር ቤት መላክ ትችያለሽ (ትችላለህ)፡፡ ገንዘብ ለመላክ የሚከፈለው ገንዘብ እንደ ሚላክበት አገር ርቀት ይለያያል፡፡ በአጠቃላይ ከ 100 አሜሪካን ዶላር እስከ 1,000 ዶላር ለመላክ እንደ ምንዛሬው መጠን 15 ዶላር ያስከፍላል፡፡
- ገንዘብ በባንክ በኩል ለመላክ ከአሰሪሽ(ህ) የባንክ ሂሳብ አገር ቤት ወደሚገኘው የራስሽ(ህ) የባንክ ሂሳብ ለማስተላለፍ ይቻላል፡፡ ገንዘብ የማስተላለፉን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ ከአገርቤት ከመነሳትሽ(ህ) በፊት የባንክ ሂሳብ መክፈት ያስፈልግሻ(ሀ)ል፡፡ ሊባኖስ ሆኖ ገንዘብ የሚልከውና በአገርሽ(ህ) ያለው ገንዘቡን ተቀባይ ባንክ ሁለቱም ለእያንዳንዱ የገንዘብ ዝውውር የአገልግሎት ማስከፈላቸውን መገንዘብ ይገባሻ(ሀ)ል፡፡ በዚህ ዘዴ ወደ አገር ቤት ገንዘብ ለመላክ ከመወሰንሽ(ህ) በፊት ምን ያህል ገንዘብ እንደሚያስከፍሉ ማወቅ ይኖርብሻ(ሀ)ል፡፡
- ገንዘቡን ወደ አገር ቤት የምትልኪ(ክ)ው በሰው አማካኝነት (በኩል)ከሆነ የምትልኪ(ክ)ው ሰው የምታምኚ(ነ)ውና የነገርሺ(ውን) የሚፈጽም መሆኑን ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

## 10. ትራንስፖርት

በቤይሩት እና በአገሪቱ የተለያዩ የመጓጓዣ ዘዴዎች አሉ፡፡

- በሊባኖስ በሚገኙ አብዛኛዎቹ ከተሞች ውስጥ አውቶብስ ለመሳፈር 1500 የሊባኖስ ሊራ ያስከፍላል፡፡
- በየአካባቢው ያሉ ሚኒባሶች 700 የሊባኖስ ሊራ የሚያስከፍሉ ሲሆን ከከተማ ውጪ

የሚሄዱ አውቶቡሶች የሚጠይቁት አነስተኛ ክፍያ 2000 የሊባኖስ ሊራ ነው።

- በአንድ ከተማ ውስጥ ያሉ ወይም ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ የሚጓዙ ታክሲዎች ዋጋ በጣም ይለያያል። ብዙ ሰዎች ባንድ ላይ የሚሳፈሩበት ታክሲ ሰርቪስ ይባላል። የግል ታክሲዎች እና ሰርቪሶች በከተማ ውስጥ እና በየከተሞች መሃል ይሰራሉ። አንድ በሰርቪስ የሚደረግ ጉዞ እንደ ርቀቱ ወይም ጊዜው ሁኔታ (የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ከሆነ) ከ 1500 እስከ 2000 የሊባኖስ ሊራ ይፈጃል። የሰርቪስ ዋጋ ረዘም ላለ ጉዞ እጥፍ ሊደርስ ይችላል፣ ይህም ሰርቪሳይን ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ዋጋውም 3000 የሊባኖስ ሊራ ነው።
- የታክሲዎች ታርጋ ቀይ ነው።



## ጠቃሚ ጥቆማዎች

- ዋጋ በየጊዜው ሊጨምር ስለሚችል ትክክለኛውን ማረጋገጥ እና እንዲቀንስ መደራደር ያስፈልጋል::
- ሰርቪስ ወይም የታክሲ ኮንትራት መፈለግሽ(ህ)ን፣ መኪናው ውስጥ ከመግባት(ህ) በፊት ለሹፌሩ መንገርና እንደምትሄጅ(ድ)በት ቦታ ርቀት መጠን የዋጋ ስምምነት ማድረግ የግድ ያስፈልግሻ(ሀ)ል።
- ወዲህ ወዲያ ስትይ(ል) ቦታው እንዳይጠፋብሽ(ህ) የምትኖሪ(ር)በትን አካባቢ በደንብ ለማወቅ ምክሪ(ር)።
- የምትኖሪ(ር)በትን አካባቢ ስሞች እወቂ(ቅ)።

- በቤቱ አካባቢ ያሉ (ለምሳሌ ሱቅ፣ ሙዚየም፣ ህንፃ፣ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት፣ ሲኒማ ቤት ወዘተ… ሊሆን ይችላል) ምልክት አድርገሽ(ህ) ያዥ(ዝ)፡፡
- ምናልባት ቦታው ጠፍቶሽ(ህ) እንዳትባዝኝ(ን) አቅጣጫ ለመጠየቅ እንድትችይ(ል) የአሠሪሽ(ህ)ን አድራሻና የስልክ ቁጥር በዐረብኛና በእንግሊዝኛ ፅፈሽ(ህ) ያዥ/ዝ፡፡

## 11. ገበያዎች

በዋና ዋና ከተሞች ልብስም ሆነ ምግብ የሚሸመትባቸው (የሚገዛባቸው) ብዙ ቦታዎች ይገኛሉ፡፡ ሆኖም በዋጋ ረገድ የተለያዩ ሊሆኑ እንደሚችሉ ተገንዘቢ(ብ)፡፡ ከውጪ ሃገር የሚገቡ ዕቃዎች በጣም ውድ ናቸው፡፡

## ውድ ሠራተኛ ሆይ

ይህ መመሪያ በሊባኖስ ለመስራትና ለመኖር እንድትለማመጂ(ድ) ሁኔታዎችን ቀላል ሊያደርጉልሽ(ህ) የሚችሉ አንዳንድ ጠቃሚ መረጃዎችን እንደሚሰጥሽ(ህ) ተስፋ እናደርጋለን፡፡ በመጨረሻ ልናረጋግጥልሽ(ህ) የምንፈልገው የሊባኖስ መንግሥት ከዓለም አቀፍ እና አገር በቀል ድርጅቶች ጋር በመተባበር ምቹ ሥራ ለሁሉም በሚል መንፈስ የግል ደህንነትሽ(ህ) እንዲጠበቅና የተሻለ የሥራ ሁኔታ እንዲፈጥርልሽ(ህ) ለማድረግ የሰሩ መሆኑን ነው፡፡ ይህም ሆኖ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን እንደ ፓስፖርትሽ(ህ)ን ራስሽ(ህ) የመያዝ፣ ከመጀመሪያው ወር አንስቶ ደመወዝሽ(ህ)ን ሙሉ በሙሉ የመከፈል፣ ለተጨማሪ ሰዓት ለሠራሽ(ህ)በት ክፍያ የማግኘት መብትሽ(ህ)ን እንዲሁም የዕረፍት ቀን የማግኘት መብቶችሽ(ህ)ን ለማስከበር አስቸጋሪ ሊሆንብሽ(ህ) ይችላል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የሊባኖስ ህብረተሰብ ግንዛቤ እንዲያገኝ ለማድረግ ሁላችንም እየጣርን ነው፣ የእናንተ ዕርዳታ ካለበት ውጤታማ እንደምንሆን ተስፋ አለን፡፡

# አባሪዎች

## አባሪ 1:- <u>የዐረብኛ ቋንቋ</u>

ዐረብኛ የሊባኖስ የሥራ ቋንቋ ነው፣ ሆኖም እንግሊዝኛና ፈረንሳይኛም ይሰራባቸዋል፡፡

ዘወትር ሊያገለግሉ የሚችሉ የአረብኛ ቃላት የሚከተሉት ናቸው::

### ሰላምታ አሰጣጥ

- ሰላም - መርሃባ
    - **መልስ** - መርሃብ ቴይን
- ደህና ሁን(ኚ) - መአ ሰላማ/አላህ ማአክ
- እንዴት አደርክ(ሽ) - ሳባህ አል - ካይር
    - **መልስ**

  (ደህና እንዴት አደርክ(ሽ) - ሳባህ አልኑር
- እንዴት አመሸህ(ሽ) - ማሳ አልካይር
    - **መልስ**

  ደህና፣ እንዴት አመሸህ|(ሽ) - ማሳ አንኑር
- ደህና እደር(ሪ) - ትስባህል ኑር
    - **መልስ**

  ደህና እደር - ዋ ኢን ሚን አህሉ
- እሺ (አዎን) - ና አም/አይዋ
- አዎ - አይዋ
- አይ(የለም) - ላ

- እባክህ(ሽ) **(ለመጠየቅ)** - ኢዛ ቢትሪድ/ኢዛ ብሬዲ (ለወንድ/ለሴት)
- እባክዎ **(በትህትና)** - ላው ሳማህት/ላው ሳማህቲ(ለወንድ/ለሴት)
- ይግቡ - ኢትፈደል/ኢትፈደሊ (ለወንድ/ለሴት)
- አመሰግናለሁ - ሹክራን/ሜርሲ
- በጣም አመሰግናለሁ - ሹክራን ከቲር

  o **መልስ**

  እኔም አመሰግናለሁ - አፍዋን ወይም ቴክራም/ቴክራሚ (ለወንድ/ ለሴት)

- አንድ ጊዜ ቆየኝ - ላህዛሚን ፋድላክ (ለወነድ/ለሴት)
- ይቅርታ - አፍዋን
- አዝናለሁ - ብልህዝን
- ችግር የለም - ማፊ ሙሽኪሊ
- ግድ የለም - ማአሌሽ
- አንዴ ቆየኝ - ላህዛ
- እንኳን ደስ ያለህ - መብሩክ
- እንዴት ነህ? - ኪፋክ?/ኪፊክ (ለወንድ/ለሴት)
- ደህና ነኝ፣አመሰግናለሁ - አልሃምዱሊላህ፤እናኒህ
- ስምህ ማነው? - ሹ-ኢስማክ?/ሹ-ኢስሚክ (ለወንድ/ለሴት)
- ስሜ - ኢስሚ....
- ስለተዋወቅዎት ደስ ብሎኛል - ሸረፍና አና መብሱት
- አገርህ(ሽ) - በለድህ ወይም በለድሽ? (ለወንድ/ለሴት)
- አገሬ - አና ሚን
- ...ትወዳለህ? - ኢን ቢቴብ? ኢንቲ ቢቴቢ? (ለወንድ/ለሴት)

- ...እወዳለሁ - አና ብሄብ
- ...አልወድም(አልፈልግም) - አና ማ ብሄብ....

## አቅጣጫ ለማወቅ

- ...በየት በኩል ነው? - ምን ዌን..?
- በዚህ በኩል ነው - ሚንሆን
- በዚህ/እዚያ - ሆን/ሆኒክ
- ፊት ለፊት - ውሽ ለውሽ
- ቅርብ - እሪብ
- ሩቅ - በይድ
- ሰሜን - ሺ ማአል
- ደቡብ - ጃኑብ
- ምስራቅ - ሻርቅ
- ምዕራብ - ጋርብ

## ድንገተኛ ሁኔታ

- እርዳኝ - ሳእድኔ
- አሞኛል - አና ማሪድ/ማሪዳ (ለወንድ/ለሴት)
- ፖሊስ ጥሩልኝ - አይቱ ሊ ፖሊስ
- ዶክተር - ዳክቱር
- ሆስፒታል - ሙሽተሽፋ
- ፖሊስ - አል ቦሊስ
- ሂድ ከዚህ - ኢምሺ/ሩህ ሚን ሆን!
- ታፍሪያለሽ(ህ) - ብትስቴሂ

## ቁጥሮች

0 ስፍር

1 ዋሂድ (ዋሃድ)

2 ትኔይን/ቲኔ ይን

3 ክሌቴ

4 አርባ

5 ኻምሴ

6 ስቴ

7 ሰበአ

8 ስሜኔያ

9 ስስኣ

10 አሽራ

11 እዳ አሽ

12 ትና አሽ

13 ክለታ አሽ

14 አርባ አሽ

15 ካምሳ አሽ

16 ስትኣ አሽ

17 ሰባ አሽ

18 ተመን አሽ

19 ታሳታ አሽ

20 አሽሪን

21 ዋኢድ (ዋሃድ)ዋ አሽሪን

30 ተላቲን

40 አርባኢን

50 ካምሲን

60 ሲቲን

70 ሰባኢን

80 ተማኒን

90 ቲሲኢን

100 ሚያ

200 ሚያ ይን

1,000 አልፍ

2,000 አልፋይን

3,000 ተለት-አለፍ

## ሰዓትና ቀን

- ስንት ሰዓት ነው? - አደይሽ ኢሳአ?
- መቼ? - ኤምቴን
- አሁን - ሃላ
- በኂላ - ባአዳይን
- (ልክ) በሰዓቱ - አል ዋኬት
- ቀደም ብሎ - ባኪር
- ረፋድ - ማቃር(ማአካር)
- ዘወትር - ኪል ዩም

- ዛሬ - አል-ዩም
- ነገ - ቡክራ
- ከነገወዲያ - ባአድ ቡክራ
- ትላንትና - ኢምባአሪክ
- ደቂቃ - ደቂቃ
- ሰዓት - ሴአ
- ቀን - እየም
- ሳምንት - ኡስቦ(ዩስቦ)
- ወር - ሻሀር
- ዓመት - ሳና
- ጠዋት - ሰባህ
- ከሰዓት በኋላ - በአድ ደኸር
- ምሽት - አሽዬ
- ሌሊት - ሌል
- ሰኞ - ተኔን
- ማክሰኞ - ተሌታ
- ረቡዕ - አል-አርበአ
- ሐሙስ - አል-ካሚስ
- አርብ - አል-ጁማአ
- ቅዳሜ - ሰብት
- አሁድ - አል-አሃድ

## ዕቃ መግዛትና አገልገሎቶችን ማግኘት

- ...እፈልጋለሁ - አና አብሃዝ...አለ
- የት ነው? - ዋይን?
- ኤምባሲ - ሳፋራ
- አየር ማረፊያ - ማታር
- ቤተክርስትያን - ኪኔሳ
- መስጊድ - ጂሚኢ
- መግቢያ - አል-ማድካል
- መውጫ - አል-ኩሩጅ
- የልብስ ንፅሕና መስጫ - አል-ጋሲል
- ሱፐር ማርኬት - ሱፐር ማርኬት
- ገበያ (ሱቅ) - ዲኬኒ (ማሃል)
- ፓስታ ቤት - ማክ ብ አል-ባሪድ
- ምግብ ቤት - አል-ማ አም
- መለወጥ እፈልጋለሁ - ባዲ ሳሬፍ...
- ገንዘብ - ማሳአሪ
- ምን ጊዜ ይከፈታል? - ኤም ቢዮፍ ህ?
- ምን ጊዜ ይዘጋል? - አም ስኪር?
- ይህ ምንድን ነው - ኹ ሄይዳ?/ሹ ሃዳ?
- ምን ያህል ነው? - አዳይሽ?
- ስንቱን - ካም ዋሂድ
- ምን ያህል ያወጣል?- ቢ አዳይሽ?

- በጣም ውድ ነው - ሃይዳ ክቲር ጋሊ
- አለ..? - ፊ.....?
- ትልቅ/የበለጠ - ከቢር/አክባር
- ትንሽ/አነስተኛ - ሳጊር/አስጋር
- ርካሽ/በጣም ርካሽ - ርኪስ/አርካስ
- ውድ - ጋሊ
- ዝግ - ምሳካር
- ክፍት - ማፍቱህ

## የግል ሕይወት ታሪክ መረጃ

- የትውልድ ቀንና ዓመት ምሕረት - ሪክ አል-ሜላደ/ዊላአድ
- የትውልድ ቦታ - መካን አል-ሜላድ/-ዊላአዳ
- ዜግነት - አል-ጄንሲያ
- ሥም - አል-ኢስም
- ፓስፖርት - ጃዋዝ አል-ሳፋር/ወይም ፓስፖርት
- ቪዛ - ቪዛ/ሺራ

## ሌሎች

- እኔ - አና
- አንተ/አንቺ - ኢን/ኢንቲ (ለወነድ/ለሴት)
- እርሱ - ሁዋ
- እርሷ - ሂያ

- እኛ - ኒህና
- እናንተ - ኢንቶ
- እነርሱ - ሂኔ
- አምጣልኝ - ጂብሊ
- ስጠኝ - ኢቲኒ
- እፈልጋለሁ - ባዲ
- ቤት - ቤት
- የአገር ውስጥ - ባላዲ
- ተራራ - ጃባል

## ትራንስፖርት

ታክሲ - ታክሲ

አውቶብስ - ባስ

ሰርቪስ - ሰርቪስ

መኪና - ሰያራ

አውሮፕላን - ጠያራ

## በዓላት

ገና/ልደት - ኢድ አል ሚላድ

አዲስ ዓመት - ራስ ኤል ሴኔ

ፋሲካ - ኢድ አል ፎሴሀ-ፓቂየስ

ስቅለት - ጀማአ አዚሚህ

ሆሳህና - ቻአኒን

ረመዳን፡- በኢስላማዊ የጨረቃ ዑደት አቆጣጠር መነሻነት፣ ሙስሊሞች ፀሃይ ስትወጣ አንስተው እስከምትጠልቅ ድረስ የሚጾሙበት ዘጠነኛው ወር፡፡

አድሃ፡- የረመዳን ወር ካበቃ ከ 70 ቀናት በኂላ የሚውል፡፡ አብርሃም ለአላህ ያቀረበውን መስዋዕት ለመዘከር ይከበራል፡፡

## ምግብ

ዳቦ - ክብዝ

ውሃ - ማይ

ጨው - ሜሌህ

ስኳር - ሱካር

ቡና - ጋህዋህ

ሥጋ - ላህሜ

ፍራፍሬ - ፋዋኪ

አትክልት - ኮድራ

ጣፋጭ ምግብ - ሄሉ

## በማዕድ ቤት ውስጥ

ብርጭቆ - ኩባያ

ስኒ - ፊንጃን

ሳህን - ሳህን

ሹካ - ሻኡኪ

ቢላዋ - ሱኪን

ማንኪያ - ማላካ

ምድጃ - ፉሬን

ፍሪጅ - በራድ

ጠረጴዛ - ውል

ወንበር - ኩርሳ (ከራሴህ)

## በቤት ውስጥ አካባቢ

መሰላል - ሰሎም

ደረጃ - ደረጃ(ድራጅ)

ባልዲ - ሳላ

የቆሻሻ ማጠራቀሚያ - ሳሌት ዘበላ

የሲጋራ መተርኮሻ - ማንፋዳ

ካውያ - መክዌ

የልብስ ማጠቢያ ማሽን - ጋሣላ

አልጋ - ስረር-ኸት

አንሶላ - ሻርኻፍ

የቫኪውም ማፅጃ - ቫኪውም ወይም ሁቨር

## አባሪ 2:- እርዳታ ስለመጠየቅ

| ሥም | ያለበት ኃላፊነት | ማግኘት የሚቻልበት አድራሻና መረጃ |
|---|---|---|
| **የመንግሥት አገልግሎት/ጠቅላላ አገልግሎት** | | |
| የሠራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር- የውጪ አገር ሠራተኞች መምሪያ | ለውጪ ዜጎች የሥራ ፈቃድ ይሰጣል | **01/55 68 29** |
| የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር- የጠቅላይ ደህንነት ዳይሬክቶሬት ጄኔራል-የውጪ ዜጎች አገልግሎት | ➢ ለሥራ የመግቢያ ቪዛ/ፈቃድ እና የመኖሪያ ፈቃድ መስጠት<br>➢ በሊባኖስ የሚገኙ የውጪ አገር ዜጎችን ይከታተላል፡፡<br>➢ የውጪ አገር ዜጎች ሲባረሩና የደህንነት ደንቦች ተጥሰው ሲገኙ አስፈላጊውን ያደርጋል፡፡<br>➢ ለውጪ ዜጎች የሚሰጠውን የመኖሪያ ፈቃድ ጉዳይ ይከታተላል፡፡<br>➢ የተለያዩ አገራት ዜጎች ወደ አገሩ ሲገቡና ሲወጡ ይቆጣጠራል፣ እንደዚሁም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ | ሠራተኞች ሆናችሁ በአካላችሁና በስሜታችሁ ላይ ጥቃት ደርሶ ከሆነ፣ ወይም የወሲብ ጥቃት ተፈፅሞባችሁ ከሆነ ይህንኑ ለጠቅላይ ደህንነቱ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ለመንገር ከፈለጋችሁ በሚከተሉት የሥልክ ቁጥሮች ወደ “ደህንነት ክፍል” ደውሉ፡፡ ይህም መሆን ያለበት ድርጊቱ በተፈፀመ በ 48 ሰዓት ውስጥ መሆን አለበት፡፡<br><br>01/61 24 01<br><br>01/61 24 02<br><br>01/61 24 05 |
| የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር- የፖሊስ ኃይል | ሕገወጥ ስደተኛ ሠራተኞችን ይከታተላል፤ እንዲሁም እነዚህን ሰዎች ወደ አገራቸው ለመመለስ የሚደረገውን ጉዞ ለማመቻቸት እንደ ፓስፖርት፣ የመኖሪያ ካርዶችን፣ (ሰርተፊኬቶችን)፣ የሥራ ፈቃዶችን የመሳሰሉ መረጃዎችንና ሌሎች ተፈላጊ ሁኔታዎችን ከሌሎች የሚመለከታቸው ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቶች ጋር በመሆን ያጣራል፡፡ | ስለ ደረሰባችሁ ማናቸውም በደል ለፖሊስ ለማሳወቅ በስልክ ቁጥር 112 ደውሉ፡፡ |

| ኤምባሴዎችና/ቆንስላዎች | | |
|---|---|---|
| ከሊባኖስ የመንግሥት ተቋሞች በተጨማሪ፣ እርዳታ በምትፈልጊ(ግ)በት ጊዜ የአገርሽ(ህ) የዲፕሎማሲታዊ ተልእኮ አባላት አንዳንድ አገልግሎቶች ሊሰጡሽ(ህ)ይችላሉ፡፡ የአገርሽ(ህ) ኤምባሲ/ቆንስላ በሊባኖስ ውስጥ አገርሽ(ህ)ን የሚወክል አካል ነው፡፡ ተግባሩም የአገሩንና የአንቺ(ተ)ን ጥቅሞች ማስከበር ነው፡፡ | | |
| የባንግላዲሽ ቆንስላ | ጄኔራል ቆንስል፡ ሚስተር መሃመድ ዳንዳን | 01/322005 የሚገኙት በጆን ኬኔዲ ጎዳና፣ በቲና ማዕከል ህንፃ 1ኛ ፎቅ፣ አይን ምሬሲ ነው፡፡ |
| የኤርትራ ቆንስላ | ጄኔራል ቆንስል፡ ሚስተር አብደላ ማትሪጅ | 01/707333 የሚገኙት በሳሚ ዛነይ ህንፃ፣ 2ኛ ፎቅ፣ ብሊስ ጎዳና፣ ከቤይሩት የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ ፊት ለፊት፣ ራስ ቤይሩት ነው፡፡ |
| የኢትዮጵያ ቆንስላ | ቆንሲል ጄኔራል፡ አቶ አሳምነው ደበሌ | 01/38 87 86 የሚገኘው በዘይድ ሕንፃ፣ 1ኛ ፎቅ ሲሆን አካባቢው ዩን ተብሎ ይጠራል፡፡ |
| የሕንድ ኤምባሲ | ጄኔራል አምባሳደር፡ ሚስተር ራቪ ታፓር | 01/786210 የሚገኘው በሰህማራኒ ህንፃ 2ኛ ፎቅ፣ በካንታሪ ጎዳና ሰሜን 31 ቡርጅ አልሙር ነው፡፡<br><br>ኢ-ሜይል፡ indembei@dm.net.lb |
| የማዳካስካር ቆንስላ | ጄኔራል ቆንስል፡ ሚስተር ማርሴል አሉ ቸዲድ | 09/44 43 33. አዲሱ ማዕከል ተሬሳ ባህር ዳርቻ |
| የፊሊፒንስ ኤምባሲና የፊሊፒንስ የውጪ ሠራተኞች ጉዳይ ፅ/ቤት (ፖሎ) | የፊሊፒንስ የውጪ ሠራተኞች ጉዳይ ፅ/ቤት ሠራተኞችና አሰሪዎችን በማስማማት ይረዳል፡፡<br><br>ቻርጅ ዲ አፌር (ጉዳይ ፈፃሚ)፡ ሚስተር ማሪያኖ ዱሚያ<br><br>የደህንነት አታሼ፡ ሚስተር ማሪዩ አር አንቶንዩ | 01/21 20 01 አሽራፊህ፣ ቻርለስ ማሌክ ጎዳና፣ ሳጌሴ ት/ቤት አጠገብ፣ ከሮድስተር ምግብ ቤት ፊት ለፊት፣ የፖ.ሣ.ቁ.136631፣ ቤይሩት ኢ-ሜይል beirutpe@dfa.gov.ph<br><br>**የአስቸኳይ ጥሪ መስመሮች ከውጪ አገር ከሆነ +9613 859430 ወይም +9613 988207 ከሊባኖስ ከሆነ 03/859430 ወይም 03/988207** |

| | | |
|---|---|---|
| የሴሪላንካ ኤምባሲ | አምባሳደር፡ ክቡር ሜራሳሂብ ማሃሩፍ | 05/924 769/64፣ የሚገኘው ሉአይዜ ውስጥ፣ ከጀምሁር አጠገብ፣ 1ኛ ና 2ኛ ፎቅ፣<br>ኢ-ሜይል slemblbn@cyberia.net.lb |
| የሱዳን ኤምባሲ | ቆንስላ ጀነራል፣ ሚስተር ሰሚር ባትቡት | 01/35 32 70 ወይም 01/35 00 57 የሚገኘው በሚንካራ ህንፃ ላይ፤ 7ኛ ፎቅ ከብሪስቶን ሆቴል ፊት ለፊት፣ ሃማራ ነው፡ |
| የቶጎ ቆንስላ | ቆንስላ ጀነራል፣ ሚስተር ጆርጅ ቡስታኒ | 09/937137 ፣ ጁኒህ |
| ኔፓል የክብር ቆንስላ ጀነራል | ሚስተር ጆ ኢሳ ኤል ኩሪ | ቴሌ ፋክስ 01/386690፣ ናዲም ጎዳና ኮሜር ሕንፃ፣ ሊባኖስ ቤይሩት<br>ኢ-ሜይል elkouryj@dm.net.lb |
| ኢንዶኒዥያኤምባሲ | አምባሳደር፣ዲማስ ሳሙድራ | ፕሬዘዳንታዊ ቤተመንግስት ጎዳና ፣ ሪዩ ቁጥር 68 ሴክተር 3፣ ፖ.ሣ.ቁ 4007 ባባዳ ሊባኖስ፣<br>ስልክ +961-5-924-682<br>+961-5-924-683<br>+961-5-924-676<br>፣ፋክስ ፣+961-5-924-678<br>ኢ-ሜይል indobay@cyberia.net.lb<br>Website URL<br>WWW.welcome.to/indobey |

| በሊባኖስ ውስጥ የውጪ ዜጋ የቤት ሠራተኛን የሚረዱ መንግሥታዊ ያልሆኑና ሌሎች ድርጅቶች | | |
|---|---|---|
| **ሥም** | **የሚሰጧቸው አገልግሎቶች** | **አድራሻ** |
| የአፍሮ-እስያ ስደተኞች ማዕከል (AAMC) (ዘ አፍሮ-ኤሽያን ማይግራንት ሴንተር) | ➢ የቤት ሠራተኞች ያላቸውን የእረፍት ቀን መጥተው እንዲያሳልፉ ቦታ ይሰጣቸዋል፡፡<br>➢ ስደተኞች የሃይማኖት ስብከትና መመሪያ የበጎ አድራጎት ድምፅ (Voice of Charity) በተሰኘ የሬድዮ ጣቢያ አማካይነት ዘወትር እሁድ ከ2፡00 ሰዓት እስከ 3፡30 እንዲሁም ዐርብ ከሰዓት በኋላ በ10 ሰዓት ያስተላልፋል ጣቢያዎቹ ኤፍ ኤም 87.5፣ ኤፍ ኤም 105.8 ና ኤፍ ኤም 106.2 ናቸው፡፡ ፕሮግራሙ የወንጌል ንባብን፣ የተከናወኑ ተግባራት መግለጫ የሚያካትት ሲሆን በተጨማሪ ለአድማጮች በየቋንቋቸው ምክር ይሰጣል፡፡<br>➢ ከስደተኛ ሠራተኞች ጋ በመተባበር በዓመት አራት ጊዜ ሕብረት(Solidarity) የተሰኘ መፅሔት ያሳትማል፡፡ | 01/33 26 01፣ የሚገኘው በቅዱስ ዮሴፍ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ 1ፎቅ ላይ፣ ከ ባሪስ አጠገብ፣ ቤይሩት ውስጥ ነው፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| የሊባኖስ ካሪታስ የስደተኞች ማዕከል (ካሪታስ ሊባነን ማይግራንት ሴንተር) | ➢ ለስደተኛ ሠራተኞችና ሌሎች የስደተኞች የምክር አገልግሎት መስጠትን፣ የሕክምና ኢንኢንሹራንስ ማግኘትን ጨምሮ በሕግና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ እርዳታ ይሰጣል፡፡<br>➢ የስደተኞችን ልጆች ትምህርት ያስተምራል፣ እንዲሁም ወደመጡበት እንዲመለሱና መልሰው እንዲቋቋሙ እርዳታ ያደርጋል፡፡<br>➢ አዲስ የመጡ ሠራተኞች እርዳታ ማግኘት እንዲችሉና ራሳቸውን እንዲጠብቁ የማለማመጃ ትምህርት ይሰጣል፡፡<br>➢ በሕገወጥ መንገድ ተነግዶባቸው የገቡ ሴቶችንና ስደተኛ ሠራተኞችን ይረዳል፣ በእስር ላይ ለሚገኙ ሠራተኞች እርዳታ ይሰጣል፡፡ | 01/50 25 50 ማዕከሉ የሚገኘው በሲን ኤል ፊል፣ ቤይሩት ነው፡፡ የአስቸኳይ ጥሪ ስልክ ከውጪ አገር ሲሆን +961 3/09 25 38 ሊባኖስ ከሆነ 03/09 25 38 ነው፡፡ |
| የፓስተሮች አፍሮ-እስያ ስደተኞች መርጃ (ዘ-ፓስቶራል ኬር ኦፍ አፍሮ-ኤሽያን ማይግራንትስ (PCAAM) | ➢ የካቶሊክ ቀሳውስት፣ ሲስተሮችና ምዕመናን ለስደተኛ ሠራተኞች የሚያደርጉት እርዳታ ያስተባብራል፡፡ ለስደተኛ ሠራተኞች የመንፈሳዊ አገልግሎት ድጋፍና የአንድነት ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋል፡፡<br>➢ የፓስተሮች አፍሮ-እስያ ስደተኞች መረጃ በየወሩ በአፍሮ-እስያ ስደተኞች ማዕከል ይሰበሰባል፡፡ በተጨማሪም አንዳንድ የሕግ የምክር አገልግሎት ድጋፍ ይሰጣል፡፡ | 01/33 76 55 የፓስተሮች አፍሮ-እስያ ስደተኞች መርጃ ፕሬዚዳንት አቡነ አንቶአን-ናቢል አንዳሪ ናቸው፡፡ ማዕከሉን የሚያስተባብሩት ቤይሩት ውስጥ ከ ባሪስ አቅራቢያ ከሚገኘው በአዲስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ኮሌጅ 1ኛ ፎቅ ውስጥ የጄስዊት ቄስ የሆኑት፣ አባ ማርቲን ማክዴርሞንት ናቸው፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| የቤይሩት የሕግ ባለሙያዎች ማህበር (የሰብዓዊ መብት ኢንስትቲዩት) (ቤሩት ባር አሶሲዮሽን) | ኢንስትዩቱ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የሕግ አገልግሎት ድጋፍ መስጠት የሚችል የሕግ እርዳታ ሰጪ ኮሚቴ አለው፡፡ | 01/48 05 51/ 01/42 39 43፣ የሚገኘው በሰብዓዊ መብቶች ኢንስቲትውት፣ ቃስር ኤል አዴል ቤይሩት-ሊባኖስ ነው፡፡ |
| ሲንዴኬት ኦፍ ሪክሩትመንት ኤጀንሲስ ኢን ሊባነን | በሊባኖስ ለሚገኙ አስቀጣሪ ድርጅቶች በሥነ ምግባርና መልካም የሥራ አፈፃፀም አንዳንድ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፡፡ | 01/61 28 08፣ የሚገኘው በባዳሮ መንገድ፣ ትራቡልሲ ህንፃ፣ 4ኛ ፎቅ፡ ቤይሩት ነው፡፡ |
| የስደተኛ ሰራተኞች ግብረ ኃይል(MWTF) | የስደተኛ ሰራተኞች ግብረኃይል(MWTF) ዋና ዓላማው በሊባኖስ የስደተኛ ሰራተኞችን ህይወት ከመነሻው ማሻሻል ነው፡፡በየሳምንቱ እሁድ በአረብኛ፤በእንግሊዝኛና በፈረናሳይኛ ቋንቋዎች በቤይሩት ሳናያህ ዚኮ ቤት ከቀኑ 6 ሰዓት 8 ሰዓት ድረስ የቋንቋ ትምህርት ይሰጣል፡፡ | Website http://mwtaskforce.wordpress.com ስልክ 00961 70 066880 Email: farahsalka@gmail.com |

| | | |
|---|---|---|
| የፀረ ዘረኝነት እንቅስቃሴ(ARM) | የፀረ ዘረኝነት እንቅስቃሴ (ARM)ዓላማው በሊባኖስ የዘረኛነት እንቅስቃሴን መቆጣጠር፤ዶኩመንት ማድረግና እርምጃ መውሰድ ሲሆን በተለይ በስደተኛ የቤት ውስጥ ሰራተኞች ላይ ያተኩራል፡፡ ስለሆነም በማንኛውም ቦታ/ሬስቶራንት/የባህር ዳርቻ/ኤጀንሲ የምትነግሩን ታሪክ ካለ፤ የቤት ውስጥ ሰራተኛ ሞትን ከሰማችሁ ቀጥሎ ባለው አድራሻ አሳውቁን፡፡farah@nasawiya.org በተጨማሪም ማናኛውም የስደተኛ ኮምዩኒቲ/ማህበረሰብ ባህላዊ ክብረበዓል ማክበር ከፈለገ የፀረ ዘረኝነት እንቅስቃሴ (ARM) አባላት ድጋፍና እገዛ ሊደርጉለት ይችላሉ፡፡ | Website<br>http://antiracismmovement.blospot.com<br>ስልክ 00961-71 421593 |
| **KAFA** | **KAFA** በሊባኖስ ሚንቀሳቀስ በሴቶች ጥቃትና መብት ጥሰት ላይ የሚሰራ አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ነው፡፡የ **KAFA** ማድመጥና ምክር ማእከል(LCC) አካላዊና ፆታዊ ጥቃት የተፈጸመባቸውን ስደተኛ ሰራተኞችን ጨምሮ ለተጠቂዎች ማሃበራዊና የህግ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ጥብቅና ይቆማል፤ጥቃት ለመፈጸሙ የፎረንሲክ የምርመራ ውጤት እንዲገኝ መምራትና መጠለያ የመስጠጥ ሥራ ይሰራል፡፡ | ተጠቂዎች KAFA 24/7 በ 03018019<br>ስልክ፡ 01 392220-1<br>አድራሻ፡ 43፤ ባዳሮ ጎዳና፤በይዱን ህንጻ፤1ኛ ፎቅ፤ቤይሩት ሊባኖስ |

## አባሪ 3:- የግል የቀን ማስታወሻ

| የግል መረጃዎች መመዝገቢያ የቀን ማስታወሻ - 1ኛ ዓመት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለሥራ የመግቢያ ቪዛ (በፓስፖርት ላይ) | የመኖሪያ ፈቃድ | የሥራ ፈቃድ | ፓስፖርት ማደስ | የመውጫ ቪዛ |
| የመጀመሪያ ቀን | | | | | |
| የመጨረሻ ቀን | | | | | |
| የማደሻ ቀን | | | | | |

| የግል መረጃዎች መመዝገቢያ የቀን ማስታወሻ - 2ኛ ዓመት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለሥራ የመግቢያ ቪዛ (በፓስፖርት ላይ) | የመኖሪያ ፈቃድ | የሥራ ፈቃድ | ፓስፖርት ማደስ | የመውጫ ቪዛ |
| የመጀመሪያ ቀን | | | | | |
| የመጨረሻ ቀን | | | | | |
| የማደሻ ቀን | | | | | |



ቀይ መስቀል 140



የእሳት አደጋ መከላከያ 125



ፖሊስ 112

## አባሪ 4:- ስለማህበራት የቅድመ-ጉዞ ሥልጠና እና በአገርሽ(ሀ) ስለሚገኙ የስደተኞች ማህበራት የሚገልፅ ጠቃሚ መረጃ



<u>ፊሊፒንስ</u>

**የፊልፒንስ የባህር ማዶ የቅጥር አስተዳደር፡-** የአገሪቱን የባህር ማዶ የቅጥር ፕሮግራም የሚገኘውን ጥቅም ለማሳደግ ኃላፊነት የተሰጠው የመንግሥት ተቋም ነው፡፡ የተሰጠው ሕጋዊ ኃላፊነት "በባህር ማዶ የሚሰሩ የፊሊፒንስ ተወላጆች ሠራተኞች ሥራ ምቹና ውጤታማ ማድረግ ነው፡፡" በተጨማሪም ከቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ክህሎት ማሳደጊያ ባለሥልጣን ጋር በቅርብ በመሥራት ለባህር ማዶ ሠራተኞች የቅድመ ጉዞ ሥልጠና ይሰጣል፡፡ ለበለጠ መረጃ http://www.poea.gov.ph/ ይጎብኙ፡፡

**የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና የክህሎት ማሳደጊያ ባለሥልጣን፡-** በፊሊፒንስ የቴክኒክና ሙያን እና የክህሎት ማሳደጊያን ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር የተቋቋመ መንግስታዊ ተቋም ነው፡፡ ለቤት ውስጥ ሠራተኞች ግምገማና ሥልጠና የተቋቋመ ማዕከላትን ሕጋዊ ፍቃድ የመስጠትና የክህሎት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶችን የመስጠት ሥልጣን ያለው ነው፡፡ የባህር ማዶ የቤት ውስጥ ሠራተኞችን የክህሎት ሥልጠናና የእውቀት ልምድን ያስፋፋል፡፡

**አድራሻ:** የሠራተኛ ጉዳይና ቅጥር መምሪያ፣ ሙራላ መንገድ፣ ጄኔራል ሉና መንገድ፣ ኢንትራሙሮስ፣ 1002 ማኒላ፣ ፊሊፒንስ፣ የአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ ሰልክ ቁጥር (+632) 887-7777 ሌሎች መስመሮች (+632) 817-40-76 እስከ 82

**የባህርዳር ሠራተኞች እርዳታ አስተዳደር:-** ከሠራተኛ ጉዳይና ቅጥር መምሪያ ጋር የተያያዘ ሆኖ የፊሊፒንስ ዜጋ ሠራተኞችንና በእርሱ ሥር የሚተዳደሩትን ሰዎች ደህንነት ለመጠበቅና ለማጎልበት ኃላፊነት የተጣለበት የመንግሥት ተቋም ነው፡፡ በስደተኞችና በሴቶች ብዝበዛ ላይ ከቅጥር በፊት መረጃ የማሰባሰብ ዘመቻ ይካሄዳል፡፡ ለፊሊፒንስ የባህር ማዶ ቅጥር ተቋም ለሚቀርቡ አቤቱታዎች የምክር፣ ተጠሪ የመሆን እንዲሁም አቤቱታዎቹን ለተገቢው አካል የማቅረብ እርዳታ በመስጠት ይረዳል፡፡

**አድራሻ:-** የባህር ማዶ ሠራተኞች ማዕከል፣ 1043፣ አውሮራ መንገድ ፣ ኩዊዞን ከተማ፣ 1108 ፊሊፒንስ፣ ስልክ 02 913 6439፣ ፋክስ 02 913 6438 http://www.owwa.gov.ph

**የሠራተኞች የቅጥር መምሪያ:-** ያለው ኃላፊነት ጠቃሚ የቅጥር ዕድሎችን ማፈላለግ፣ የሰው ኃይልን ማሠልጠን፣ ሠራተኞችን መንከባከብና ደህንነታቸውን መጠበቅ፡፡

አድራሻ፤ ለአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ (632) 527-8000, http://www.dole.gov.ph/

**የተባበሩት የፊሊፒንስ ባህርተኞች:-** በፊሊፒንስ ውስጥ ያለ የሠራተኞች ፌዴሬሽን ነው፡፡ እርስ በእርስ ለመረዳዳት፣ የጋራ ደህንነትን ለመጠበቅና የአባላቱን የሞራል፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ሁኔታ ለማሳደግ የተቋቋመ የሰራተኞች ማህበር ነው፡፡ የምዝገባ ቁጥር 11863 እ.ኤ.አ. በኦክቶበር 2, 2000 ዓ.ም ከፊሊፒንስ የሠራተኞች ጉዳይ መምሪያ እውቅና የተሰጠው ነው፡፡

**አድራሻ:** 4 ኤፍ የቢሮ ቁጥር 402 ጌዲስኮ ቴሪስ 1148፣ ሮክስስ ብሎቫርድ፣ ኤርሚ፣ ማኒላ ወይም ስልክ 524-2336 እና 524-4888

**ካካምፒ፡** በማህበረሰብ ላይ ትኩረት የሚያደርግ የፊሊፒንስ ዜጋ የባህር ማዶ ሠራተኞች ቤተሰቦችና ከስደት ተመላሾች ድርጅት ነው፡፡ ካካምፒ የተቋቋመው በባህር ማዶ የሚሰሩ የፊሊፒንስ ዜጎችን መብትና ደህንነት ለማስከበር በባህር ማዶ ስደት ምክንያት ለሚፈጠሩ ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት ነው፡፡ ካካምፒ በማደራጀት፡ ለመብቶች በመሟገት፣ ክስ በመመስረት እንዲሁም በተቋማት መካከል ቅንግት የመፍጠር ሥራዎችን ያከናውናል፡፡ የቤተሰቦች ሥርዓትንና በጉዳዮች ላይ የመወሰን ሥልጣናቸውን ለማሳደግ የተቀናጀ ፕሮግራም በማካሄድ የስደተኛ ቤተሰቦችን ችግሮችና ፍላጎቶች ለማሟላት ይጥራል፡፡

**አድራሻ፡** ካካምፒ የፖ.ሣ.ቁ. ኤስ ኤም.193 1008 ፣ ስታ ሜሳ ማኒላ፣ ፊሊፒንስ ስልክ +632 435-4584 ቴሌ ፋክስ+632 921-5810 ኢ-ሜይል kakammpi@skyinet.net

**የፊሊፒንስ ስደተኞች መብት ተመልካች፡-** ውጪ አገር ሂዶ በመሥራት ሂደት ውስጥ፡ በፊሊፒንስም ሆነ በውጪ የፊሊፒንስ የስደተኞችን መብቶች ለማሳወቅ፣ ለመጠበቅና ለማስከበር በ1987 ዓ.ም የተቋቋመና ሕጋዊ ምዝገባ ያለው የሲቪል ማህበረሰብ ኔትርትክ ተቋም ነው:: ማዕከሉ የፊሊፒንስ ስደተኛ ሠራተኞችንና በተሰቦቻቸውን መብቶች ለማሳወቅ ለማክበርና ለሟሟላት ሲባል የትምህርት የማሳመን እንዲሁም የመቆጣጠር ተግባራት የተጠቀሱት ሰዎች ወደውጪ ከመሄዳቸው በፊት፤ በሚሄዱበት ወቅትና በሚመለሱበት ወቅት ያከናውናል፡፡

**አድራሻ** : 72 ማ ሂሚክ ጎዳና፣ ቲጨርስ ቪሌጅ ኩይዞን ከተማ፡ ፊሊፒንስ፡ ስልክ/ፋክስ +632 433 0684' 920 5003 ኢ-ሜይል cma@tri-isys.com, http://www.pmrw.org/

**ጋብሪኤላ ኮሚሽን ኦን ኦቨርሲስ ፊሊፒንስ**

**የባህር ማዶ ፊሊፒንስ ዜጎች የገብርዔል ኮሚሽን**

**አድራሻ:** 35 ስካውት ዴልጋዶ ጎዳና፣ ሮክሳስ አውራጃ፣ ኪውዞን ከተማ፣ ስልክ 374-3452 ፋክስ 374-4423፣ የሚመለከተው ግለሰብ ስም ሮዛሪዩ ፖዲላ

| |
|---|
| **ስካላብሪኒ የሥደተኛ ማዕከል**<br><br>**አድራሻ:** 4 :13ኛ መንገድ አዲሱ ማኒላ፣ 1112 ኪውዞን ከተማ የ ፓ.ሣ.ቁ.10541 ብሮድዌይ ሴንትሩም፣ ስልክ (63-2) 724-3512 ወይም (63-2) 721-4296 ኢ-ሜይል smc@smc.org.ph |
| **አሲሎ ደ ሳን ቪንሴንት ዲ ፓል**<br><br>**አድራሻ: ፖኮ፣ ማኒላ፣ ስልክ** 523-5264/522-1643 **ፋክስ** 522-8696<br>**ኢ-ሜይል** mailto:asilomla@yahoo.com ወይም asilomla@yahoo.com |
| **ዳዮሲስ ኦፍ ሰን ፌርዲናንዶ ኦፍ ላ ዩኒየን (የአዲስ ፌርዲናንድ ሰበካ ጉባዔ)**<br><br>**አድራሻ፤ ሳንቲያጎ፣ ባዋን ስልክ** (072) 705-0553 **ፋክስ** 0918-920-3578 **ኢ-ሜይል** ezrazre@yahoo.com |
| **ኮሌጅዬ ዴል ሳግራዳ ኮራዞን ዲ ጂስስ (የኢየሱስ ........ ኮሌጅ)**<br><br>አድራሻ: ጀኔራል ሂዩስ ጎዳና፣ ኢሊዮሎ ከተማ ስልክ (033) 3 36-94 08 ፋክስ (033) 3 37-4654 ኢ-ሜይል srbecca@yahoo.com |



**በስሪላንካ**

**በስሪላንካ የቅጥር ቢሮ፡-** ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ለሚሄዱ ያልሰለጠኑ ሴት የቤት ውስጥ ሠራተኞች የቅድመ-ጉዞ ወይም የማለማመጃ ሥልጠና ፕሮግራም በቤት አያያዝ ላይ ያካሂዳል :: ትምህርቱ ለ 21 ቀናት ይሰጣል፡፡

**አድራሻ:** 234 ዴንዚል ኮቤካዱዋ ማዋ፣ ከስዋ፣ ባ ራሙላ ስሪላካ ስልክ (094) 11 2864101

**የስደተኞች አገልግሎት ማዕከል፡-** ውጪ አገር ሄደው የሚሰሩ ሠራተኞችን ለመርዳት የቆመ የሠራተኛ ማህበር ነው፡፡

**አድራሻ:** 10 ካውንስል መንገድ፤ ዴሂዋላ፣ ስልክ 713 – 386

**ሴቲክ-ካሪታስ ካንዲ፡-** ካቱ ጋስቶ መንገድ፣ ካንዲ፣ ስልክ +94773513015 ሌላ ስልክ +94814471613 ፋክስ +94812222775 ኢ-ሜይል setik@sltnet.lk

**የጉድ ሼፐርድ ሰበካ ጉባዔ (ኮንግሪጌሽን)** 133 ፣ አናንዳራጃካሩና ማዋ ኮሎምቦ 10:: ስልክ +94112930255' ስልክ +94112932575.

**ሴዴክ ካሪታስ ስሪላንካ** : 133 ኪ.ንሲ. መንገድ፣ ኮሎምቦ 08 ስልክ +9411 2691885 ኢ-ሜይል kathflem12@yahoo.com

**ስሪላንካ ካቶሎክ ናሽናል ኮሚሽን ፎር ማይግራንትስ (የሲሪላንካ ካቶሊክ ብሔራዊ የስደተኞች ኮሚሽን)** : 11 ፣ ቦሬላ ክሮስ መስቀለኛ መንገድ 8:: ኢ-ሜይል slcncmigrants@sltnet.lk

 **በኢትዮጵ ያ**

**ጉድ ሼፐርድ ሲስትር፡-** ቦሌ መንገድ፣ አዲስ አበባ፣ ስልክ/ፋክስ+251-11 5 -513062
**ካሪታስ ኢትዮጵያ፡-** አዲስ አበባ ኢትዮጵያ +251-11 1- 55 03 00
ኢ-ሜይል ECS@Telecom.net.et

 **በኤርትራ**

ካሪታስ ኤርትራ፡ አስመራ፣ ኤርትራ፣ ስልክ +291 1 15 12 74/ 12 50 00 ፋክስ +291 1 15 11 86 ኢ-ሜይል ercsec@eol.com.er ወይም kimehret@gemel.com.er

 **በፓኪስታን**

ካሪታስ ፓኪስታን ፡ 23/3 ሬስ ኮርስ መንገድ፣ ላሆር 0092-42-6315584' ፋክስ 0092-42-6368704 ኢ-ሜይል caritasred@yahoo.com

 **በኔፓል**

ካሪታስ ኔፓል፡ ዶቢ,ጋት፣ ላሊፑር ካትማንዱ ስልክ +977-1-5538172/977-1-5543726
ኢ-ሜይል caritas@mail.com.np

 **በሕንድ**

ካሪታስ ሕንድ፡ ሲ ቢ ሲ አይ ማዕከል ፣ ኒው ዴልሂ ፣ 110001' ከጎሌዳካና ፊት ለፊት
ኢ-ሜይል director@caritasindia.org

## <u>የእኔ አስፈላጊ አድራሻዎች</u>

| | |
|---|---|
| | |
| | |
| | |

## አባሪ 5:- የቤት ውስጥ መገልገያ መሣሪያዎችን፣ ማሽኖችንና የፅዳት መሣሪያዎችን ያለ ስጋት መጠቀም

አንድ አዲስ ሥራ ስትጀምሪ(ር) ለመለማመድ ሦስት ወራት ይወስድብሻ(ሀ)ል፡፡ የቤት ውስጥ ሠራተኛ እንደሆንሽ (ህ) የቤት ውስጥ መገልገያ መሣሪያዎችን፣ ማሽኖችንና የፅዳት ዕቃዎችን በሙሉ አደጋ በማያስከትል ሁኔታ መጠቀም መቻል አስፈላጊ ነው፡፡ እያንዳንዱ አሠሪ የተለያዩ ፍላጎቶችና ልምዶች ይኖሩታል፡፡ ስለዚህ አሰሪሽ(ህ)ን በቤት ውስጥ መገልገያ መሣሪያዎች፣ ማሽኖችና የፅዳት ዕቃዎች እንዴት መጠቀም እንደሚቻል እንዲያስተምርሽ(ህ) መጠየቅ አለብሽ (ህ)፡፡

## አሰሪሽን (ህ)ን መጠየቅ ስለሚያስፈልግባቸው ሁኔታዎች አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮች እነሆ፡-

| | |
|---|---|
|  | **በቤት ውስጥ**<br>- የኤሌክትሪክ መስኪያዎችን አደጋ በማያስከትል ሁኔታ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል፡፡<br>- መስኮቶችን ፣ ስገነቶችንና ሻተሮችን እንዴት መዝጋት እንደሚቻል<br>- በሮች እንዴት እንደሚዘጉ<br>- የምድጃ ጋዝ ኤሌክትሪክና የውሃ ቧንቧ እንዴት እንደሚዘጋ<br>- መጋረጃዎችን፣ ወለሎችን፣ ምንጣፎችን፣ መስኮቶችን እንዴት ማጠብ እንደሚቻል<br>- ለእያንዳንዱ ዕቃ ምን ዓይነት ኬሚካል ወይም የማጠቢያ ሳሙና መጠቀም እንደሚያስፈልግ<br>- የቤት ውስጥ ዕቃዎችን እንዴት መጠራረግ እንደሚቻል<br>- በቫኪውም ማጽጃ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል |
|  | **በማዕድ ቤት ውስጥ**<br>- ምግብ እንዴት እንደሚቀመጥ<br>- ቆሻሻ የት እንደሚጣል<br>- ማቀዝቀዣን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል<br>- በዝግ ምድጃ፣በማይክሮ ዌቭ፣ በስሊንደር በኤሌክትሪክ ማፍያ፣ በሚክሰር፣ በዳቦ መጥበሻና በቡና ማሽን ወዘተ.... እንዴት መጠቀም እንደሚቻል |

<table>
<tr>
<td></td>
<td>በመኝታ ቤት<br>
<ul>
<li>አልጋ እንዴት እንደሚነጠፍ</li>
<li>አንሶላ መቼ እንደሚቀየር</li>
</ul></td>
</tr>
<tr>
<td></td>
<td>ልብሶች<br>
<ul>
<li>ልብስ እንዴት እንደሚታጠብ፡- በእጅ፣በማሽን</li>
<li>በልብስ ማጠቢያ ማሽን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል፡-(እንዴት ለስራ እንደሚዘጋጅ፣ የሙቀት መጠን ማስተካከል፤ ምን ያህል የዱቄት ሳሙና እና ማለስለሻ መርዝ እንደሚበቃ)</li>
<li>የሚታጠቡ ልብሶችን በቀለማቸው እንዴት ለይቶ ማሰናዳት እንደሚቻል</li>
<li>እርጥብ ልብሶችን የትና እንዴት ማስጣት እንደሚቻል</li>
<li>የካውያ አጠቃቀም</li>
<li>የተተኮሱ ልብሶችን እንዴት ማጣጠፍና የት ማስቀመጥ እንደሚቻል</li>
</ul></td>
</tr>
</table>

# አባሪ 6:- <u>ለህይወት የሚያስፈልጉ ክህሎቶች</u>

## ጊዜን በአግባቡ መጠቀም



### ጠቃሚ ጥቆማዎች

ጊዜሽ/ህ/ን በአግባቡ ተጠቀሚ/ም፡፡ ቀድመሽ/ህ ምን እንደምትሰራ/ሪ፤ የበለጠ ጊዜና ጉልበት የሚፈልገውን ሥራ ለዪ/ይ፡፡ ያወጣሽ/ከ/ው ቅደም ተከተል ከተምታታብሽ/ህ  አሰሪሽ/ህ/ን የትኛው መቅደም እንዳለበት ጠይቂ/ቅ፡፡ እረፍት አድርጊ፤አስብ.....

## አለመግባባትን ማስወገድ



### ጠቃሚ ጥቆማዎች

እርስ በእርሱ የሚቃረን ትእዛዝ ካጋጠመሽ/ህ አሰሪሽ/ህ/ን በትክክል ምን እንደሚፈልጉ ጠይቂ/ቅ፡፡ አትጩሂ፤ አትቆጪ/ም፡፡ በእርጋታና በግልጽ ለማስረዳት ሞክሪ/ር፡፡

## አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ማሳለፍ



### ጠቃሚ ጥቆማዎች

እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ካጋጠሙሽ/ህ የተሻለው መንገድ አሰሪሽ/ህ የውል ግዴታውን እንዲወጣ ማሳሰብ ነው፡፡ ለምሳሌ፡-በየወሩ፤በጊዜውና ሙሉ ክፍያ መክፈል...፡፡ አሰሪሽ/ህ የማይከፍልሽ/ህ ከሆነ ግን ለእርዳታ ማሳወቅ አለብሽ/ህ፡፡

**በአደጋ ጊዜ እንዴት መሆን እንዳለብሽ/ህ**



**ጠቃሚ ጥቆማዎች**

ማንም ሰው በአንቺ ላይ እድል እንዲኖረው አታድርጊ፡፡ ከማታውቂው ወንድ ጋር ወዳጅ መስለሽ ለመታየት አትጣሪ፡፡ አስቸጋሪ ሁኔታ ካጋጠመሽ በአንቺና ሊያጠቃሽ በሚሞክረው ሰው መካከል ርቀት ለመፍጠር ሞክሪ፡፡ ከመኪናው ውጪ፤ጩሂና እርዳታ ጠይቂ፡፡

## አባሪ 7:- <u>የውጭ ሀገር የቤት ሰራተኞች የስራ ቅጥር ውል</u>

### የሊባኖስ ሪፐብሊክ መንግስት የሰራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር

### የውጭ ሀገር የቤት ሰራተኞች የስራ ቅጥር ውል

**ተዋዋዮች፡-**

**አንደኛ ተዋዋይ(ቀጣሪ)**

ሙሉ ስም ..................................... ዜግነት ...............................................

የትውልድ ቦታ........................... የመኖሪያ ቦታ .....................................

የቤተሰብ ሁኔታ......................... የተመዘገቡበት ቦታ .................................

መታወቂያ/ግላዊ የምዝገባ ሰርተፍኬት .............................

አድራሻ ......................................... ስልክ .................................................

**ሁለተኛ ተዋዋይ(ተቀጣሪ)**

ሙሉ ስም ................................. ዜግነት .............................................

የፓስፖርት ቁጥር......................... የተሰጠበት ቀን...................................

የሚያበቃበት ቀን.......................... የትውልድ ቦታ...................................

የቤተሰብ ሁኔታ .......................... የመኖሪያ ቦታ ...................................

አንደኛ ተዋዋይ(ቀጣሪ) ልምድና ችሎታ ያለው/ያላት እና በሙሉ አቅሙ የሚሰራ/የምትሰራ ተወዳዳሪ ሰራተኛ መቅጠር ይፈልጋል፡፡

ሁለተኛ ተዋዋይ(ተቀጣሪ) በዉሉ ቀጥሎ የተመለከቱትን ያሟላል፡፡

በሊባኖስ ህግ መሰረት ሁለቱ ተዋዋዮች ይህን ውል ለመፈጸም ተስማምተናል፡፡

ሁለቱ ተዋዋዮች ቀጥሎ በተመለከቱት የውል ግዴታዎች ለመገዛት ተስማምተናል፡፡

1. የዚህ ውል መግቢያ የውሉ አካል ነው፡፡
2. አንደኛ ተዋዋይ ሁለተኛዋ/ው ተዋዋይ በቤት ውስጥ ሰራተኛነት እንዲሰሩለት ተስማምቷል፡፡ ሁለተኛ ተዋዋይ ወገንም በዚህ ውል መሰረት በቤት ውስጥ ሰራተኛነት ለማገልገል ተስማምቷል፡፡
3. አንደኛ ተዋዋይ ከመኖሪያ ቤቱና ከተጠቀሰው ስራ ውጪ ለማሰራት አይችልም፡፡
4. ውሉ የሚጸናው ለአንድ ዓመት ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ሊታደስ ይችላል፡፡
5. ይህ ውል የሚጸናው ሁለቱ ተዋዋዮች በውልና ማስረጃ ፊት ቀርበው ሲፈራረሙ ነው፡፡ ውሉ የ 3 ወር የሙከራ ጊዜንም ይጨምራል፡፡
6. አንደኛ ተዋዋይ ለሁለተኛ ተዋዋይ የተስማሙበትን ደመወዝ................. ያህል ገንዘብ በየወሩ መጨረሻ ላይ ሳያዘገይ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ ደመወዙ በጥሬ ገንዘብ ለሁለተኛው ተዋዋይ ሊከፈል ይችላል፡፡ አልያም በሁለቱም ተዋዋዮች በተፈረመበት ደረሰኝ ወይም በሁለቱም ተዋዋዮች ፊርማ በባንክ ሊከፈል ይችላል፡፡
7. ሁለተኛ ተዋዋይ ስራውን ያለመለገም፤ በታማኝነት፤ የስራ መመሪያ፤ልማድና ስነምግባር እንዲሁም የቤቱን ነጻነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ከአንደኛ ተዋዋይ በሚሰጠው ትእዛዝ መሰረት የማከናወን ግዴታ አለበት፡፡
8. አንደኛ ተዋዋይ የሁለተኛ ተዋዋይን ጥያቄ ማሟላት፤ምቹ የስራ ሁኔታ

መፍጠር፤እንደ ምግብ፤ ልብስ፤ክብሩን የሚመጥን ማደሪያና የግል ነጻነቱን በማክበር ፍላጎቶቹን ማሟላት አለበት፡፡

9. በሊባኖስ እውቅና ካለው የኢንሹራንስ ኩባንያ የሊባኖስ የሰራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር ያወጣውን መስፈርት በሚያሟላ መልኩ አንደኛ ተዋዋይ ለሁለተኛ ተዋዋይ የህክምና ወጪውን መሸፈን አለበት፡፡

10. አንደኛ ተዋዋይ በራሱ ወጪ ለሁለተኛ ተዋዋይ የሥራና የመኖሪያ ፈቃድ ማውጣት አለበት፡፡ ሁለተኛ ተዋዋይ ለእርሱ እስከሰራለት ድረስ ፍቃዱን የማሳደስ ግዴታም አለበት፡፡

11. አንደኛ ተዋዋይ ለሁለተኛ ተዋዋይ ተከታታይ ላልሆኑ 10 ሰዐታት የሚሰራበትን ጊዜ መወሰን አለበት፡፡ በምሽትም ለተከታታይ 8 ሰአታት የእረፍት ጊዜ ማመቻቸት አለበት፡፡

12. አንደኛ ተዋዋይ ለሁለተኛ ተዋዋይ በሳምንት ለተከታታይ 24 ሰአታት የሚያርፍበት ጊዜ ሊሰጠው ይገባል፡፡ የእረፍቱ አጠቃቀም በተመለከተ ሁለቱ ወገኖች ሊስማሙ ይችላሉ፡፡ ሁለተኛ ተዋዋይ በዓመት ለ 6 ቀናት የማረፍ መብት አለው፡፡ ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ስለጊዜው፤ ስለአጠቃቀሙና ስለጥቅሞቹ ሊስማሙ ይችላሉ፡፡

13. በዚህ ውል አንቀጽ 16 ከተመለከተው ውጪ አንደኛው ተዋዋይ ለሁለተኛ ተዋዋይ የመሄጃና የመመለሻ የአውሮፕላን ትኬት ይችላል፡፡

14. አንደኛ ተዋዋይ ሁለተኛ ተዋዋይ የስልክ ጥሪዎችንና መልዕክቶችን እንዲቀበል መፍቀድ አለበት፡፡ ሁለተኛ ተዋዋይ በወር ከአንድ ጊዜ በላይ ካልሆነ በቀር ዘመዶቹን ለማግኘት የሚደርገውን የስልክ ጥሪ ወጪ የሚችለው አንደኛ ተዋዋይ ይሆናል፡፡

15. ሁለተኛ ተዋዋይ በስራ ላይ እያለ ወይም ከስራ ጋር በተያያዘ ካመመው የህክምና ማስረጃ በማምጣት ግማሽ ወር ከሙሉ ክፍያ ጋር እንዲሁም ግማሽ ወር ከግማሽ

ክፍያ ጋር የህክምና እረፍት ያገኛል፡፡

16. አንደኛ ተዋዋይ ውሉን ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊያቋርጥ ይችላል፡፡

ሀ/ ሁለተኛ ተዋዋይ የአንደኛ ተዋዋይ ወይም የቤተሰብ አባላቱን ጥቅም ለመጉዳት ሆን ብሎ ወይም አውቆ ስህተት ከሰራ ወይም አደጋ ከፈጠረ ወይም ከተሳደበ፤

ለ/ በሊባኖስ ህግ መሰረት የሚያስቀጣ ድርጊት ከፈጸመ፤ ሁለተኛ ተዋዋይ ወደ ሀገሩ የመመለሻ ትኬቱን በራሱ ወጪ በመሸፈን ከሊባኖስ ሊባረር ይችላል፡፡

17. ሁለተኛ ተዋዋይ ውሉን ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊያቋርጥ ይችላል፡፡

ሀ/ አንደኛ ተዋዋይ ወገን ለተከታታይ 3 ወራት ደመወዙን ሳይከፍለው ሲቀር፤

ለ/ አንደኛ ተዋዋይ ወገን ወይም የእርሱ ቤተሰብ አባላት ወይም በቤቱ የሚኖር ሌላ ሰው ከመታው፤ ከሰደበው፤ወሲባዊ ጥቃት ከፈጸመበትና በፎረንሲክ የህክምና ማስረጃና በምርመራ ተረጋገጦ ለፖሊስ ወይም ለሰራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር ከቀረበ፤

ሐ/ አንደኛ ተዋዋይ ወገን ሁለተኛውን ተዋዋይ ወገን ያለፈቃዱ ቀጥሮት ከሆነ፤ አንደኛ ተዋዋይ ወገን ሁለተኛውን ተዋዋይ ወገን ወደ ሀገሩ የሚመለስበትን የመመለሻ ትኬቱን በራሱ ወጪ እንዲሸፍን ይገደዳል፡፡

18. በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል በውሉ የተነሳ አለመግባባት ከተፈጠረ የሰራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር በማስማማት አለመግባባቱን ሊፈታው ይችላል፡፡

19. ሁለቱን ተዋዋይ ወገኖች ማስማማት ካልተቻለ ግን ተበደልኩ የሚለው ወገን ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ሊወስደው ይችላል፡፡

20. የዚህ ስምምነት የአረብኛ ቅጂው በውልና ክብር መዝገብ ፊት በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መፈረም ያለበት ሲሆን በሁለተኛ ተዋዋይ ቋንቋ እየተዘጋጀም ይገኛል፡፡ እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን የራሱን ቅጂ/ኮፒ ሊያገኝ ይችላል፡፡

አንደኛ ተዋዋይ(ቀጣሪ)

ሁለተኛ ተዋዋይ(ተቀጣሪ)

| ለውልና ክብር መዝገብ |
| --- |
| |

ይህ መምሪያ የተዘጋጀው በባለሙያዎች ቡድን ነው። ሚስ ኢማኑኤላ ፖዛን፤ሚስ ሲሜል ኤሲም፤ሚስ ጆዬት በየነ፤ሚስ ራና ራዬስ፤ሚስማሪ ኖኤል አቢ ያጊ፤ሚስ ሳና አቡ ስሌማን፤ሚስ ጊዳ ጋንዱር፤ሚስተር ነቢል አብዶ እናሚስተር መንሱር ኦሜራ መረጃዎችን በመሰብሰብ ረቂቁን በማዘጋጀት፤ በመከለስና ኤዲት በማድረግ አስተባበረዋል።

ሚስተር አብደላ ራዙቅ፤ሚስተር ፋውዚ አል ሃጂ ሀሰን፤ሚስ ማይ ሰአብ፤ሚስተር አዲል ዱቢያን፤ሚስ ማርሊን አታላህ፤ሚስ ሱዛን ሳብራ፤ሚስ ናዝሃ ሻሊታ፤ሚስተር ነቢል ኢስቢር እና አሊ ቤሮ ከሰራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር ፤ ሚስ ሃላ አቡ ሳምራ ከፍትህ ሚኒስቴር፤ ሚስተር አቢር አብድሰመድ ከማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ሚስተር ሳሊም ባዱራ ከውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ሚስተር ኤሊ አስማር ከሀገር ውስጥ የጸጥታ ኃይሎች፤ሚስ አማል አል ወሃቢ ከአጠቃላይ ጸጥታ ዳይሬክተር ጀነራል፤ሚስ ኤልሳቤጥ ዘካርያ ሲዩፊ ከቤይሩት ጠበቆች ማህበር(ከሰብአዊ መብት ኢንስቲትዩት)፤ሚስተር አሊ አሚን ከውጪ ሰራተኖች ቀጣሪ ኤጀንሲ፤ሚስ ናጂላ ቻሃዳ ከካሪታስ ሊባን የውጭ ማእከል፤አባ ማርቲን ማክደርሞት እና ሚስተር ሮናልድ ታዋቅ ከአፍሮ ኤስያ ስደተኖች ፓስቶራል ኮሚቴ፤ሚስ ናዳ አል ናሽፍ ከአለምአቀፍ ስደተኖች ድርጅት የአረብ ሀገራት ክልላዊ ጽ/ቤት፤ሚስተር ኒዳል አል ጁርዲ ከተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ከፍተኛ ኮሚሽን የመካከለኛው ምስራቅ ጽ/ቤት ለመምሪያው ጠቃሚ ግብዐት ያበረከቱ ናቸው።

በተለይ ሚስ ናጅላ ቻሃዳ፤ ሚስ ራኒያ ሆካየም፤እንዲሁም ኤዛቤል ሳዴህ ፋጋሊ ከካሪታስ ሊባኖስ የስደተኞች ማእከል ላበረከቱት ልዩ ቴክኒካው እርዳታ የተለየ ምስጋና ይገባቸዋል።ሂዩማና ራይትስ ዎችን፤ አለምአቀፍ የስደተኖች ድርጅትን፤የተባበሩት መንግስታት የሴቶች ፈንድ ክፍለ አህጉራዊ ጽ/ቤትን እና ካፋን ጨምሮ በሊባኖስ የሚገኙ

የፊሊፒንስ እና የስሪላንካየዲፕሎማቲክ ሚሲዮን አባላት አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡አያሌ የዓለም ስራ ድርጅት አህጉራዊ፣ ክፍለ፣ አህጉራዊና የየሀገራቱ ጽ/ቤት ሰራተኞች ይህንን መመሪያ በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ ብዙ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ አይ. ኤል. ኦ - አድስ አበባ፣አይ. ኤል. ኦ - ባንኮክ፣ አይ. ኤል. ኦ - ኮሎምቦ፣ አይ. ኤል. ኦ -ሃኖይ፣አይ. ኤል. ኦ -ካትማንዱ፣አይ. ኤል. ኦ - ማኒላ፣አይ. ኤል. ኦ - ኒው ዴልሂ፣አይ. ኤል. ኦ -ቱሪን፣ ዓለም አቀፍ የማሰልጠኛ ማእከል እንዲሁም ከዋናው መስሪያ ቤት መምሪያዎች የስርአተ ፆታ ቢሮን፣ አክትራቭን፣ ማይግራንትስን፣ ኖርምስን፣ትራቬየልን፣ዲክሌሬሽንን እና ስኪልስና የቅጥር ጉዳይ ጽ/ቤትን ጨምሮ ያላቸውን ጊዜ፣ እውቀት፣ ሃብትና በሚያውቋቸው ሰዎች ጭምር አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

መመሪያውን በማንበብና አስተያየት በመስጠት አስተዋጽኦ ላደረጉ የዓለምአቀፍ የስደተኖች ድርጅት የስራ ኃላፊዎች የተለየ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ ሚስ ኤሊን ሀስፔልስ ከአይ. ኤል. ኦ - ባንኮክ፣ሚስ ግሎሪ ሞሪኖ ፎንቴስ ከአይ. ኤል. ኦ - ማይግራንት ጄኔቫ፣ሚስ ክርስቲን በህረንዲት እና ሚስ ናጅዋ ካሳይፊ ከአይ. ኤል. ኦ - የአረብ ሀገራት ክልላው ጽ/ቤት፣ ሚስ ካትሪን ላንዱይት ከአይ. ኤል. ኦ - ኖርሜስ ጄኔቫ፣ሚስ ሄልዳ ቲዳልጎ ከአይ. ኤል. ኦ - ማኒላ፣ሚስ ፐራሞ ዊራስኬራ ከአይ. ኤል. ኦ - ኮሎምቦ፣ክርስቲና ሆልምግሪን ከአይ. ኤል. ኦ - አዲስ አበባ፣ እንዲሁም ሚስ ኒሉፈር ሙኪፎር ከአይ. ኤል. ኦ - ቱሪን ላበረከቱት ልዩ አስተዋጽኦ እናመሰግናቸዋለን፡፡